# ወንጌላት

ትምህርት
ሦስት

## የማርቆስ ወንጌል

ተርጓሚ፥ እሸቴ በለጠ

THIRD MILLENNIUM
MINISTRIES

Biblical Education. For the World. For Free.

# እናስተዋውቅዎ

የሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1997 ዓ.ም. ተመሠረተ፡፡ ይህ አገልግሎት አትራፊ ያልሆነ ድርጅት ሲሆን፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎችን ለመላው ዓለም በነጻ ለማዳረስ የተቋቋመ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውን ጤናማ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ - መሠረት ያለው ክርስቲያናዊ የአመራር ስልጠና ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት፣ ምንም ዓይነት የስልጠና ግብዓቶች የማግኘት እድል ለሌላቸው ክርስቲያን መሪዎች የሴሚነሪ ሥርዓተ-ትምህርቶችን በማዘጋጀት እናሰራጫለን፡፡ ሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ በመላውም ዓለም ለሚገኙ ክርስቲያን መሪዎችና ፓስተሮች የተመጣጠነ ዋጋ ያለው፣ በደጋፊዎች የሚታገዝ፣ ለተጠቃሚው ምቹ፣ በልዩ ልዩ የመገናኛ ብዙሃን ዘዴዎች የታገዘ ሥርዓተ-ትምህርት በአምስት ቋንቋዎች (በእንግሊዝኛ፣ በስፓኘ፣ በራሺያኛ፣ በማንዳሪን ቻይንኛ እና በአረብኛ) አስተርጎሞ አሰራጭቷል፡፡ ሁሉም ትምህርቶች የተጻፉት፣ የተዘጋጁት እና የታተሙት በአገልግሎቱ ውስጥ ሲሆን በ The History Channel©. In 2009 ካሉት ጋር በቅርፅና በጥራት ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ የሰርድ ሚሊኒየም ሥራ ማለትም ጥራት ላለው የማስተማሪያና የአኒሜሽን የቪዲዮ ፕሮዳክሽን ሥራዎቹ ሁለት የቴሊ አዋርድ ሽልማቶችን ተቀብሏል፡፡ የማስተማሪያ ግብዓቶቻችን በዲቪዲ፣ በህትመት፣ በኢንተርኔት ማስተላለፊያ ዘዴዎች፣ በሳተላይት የቴሌቪዥን ስርጭት፣ በራዲዮና በቴሌቪዥን ስርጭቶች ለማቅረብ በሚያስችል መልክ የተቀረፁ ናቸው፡፡

ስለ አገልግሎታችን የበለጠ መረጃ ለማግኘትና እንዴት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን እንደምትችሉ ማወቅ ከፈለጋችሁ፣ www.thirdmill.org የተሰኘውን ድረ-ገጽ ይጎብኙ፡፡

## ማውጫ


1. **መግቢያ**
2. **ዳራ**
   - 2.1 ጸሀፊ
     - ሀ. ትውፊታዊ አመለካከት
     - ለ. ግላዊ ታሪክ
   - 2.2 ቀደምት ተደራሲያን
     - ሀ. የመጀመሪያዪቱ ቤተክርስቲያን ምስክር
     - ለ. የወንጌሉ ዝርዝሮች
   - 2.3 ወቅት
     - ሀ. ቀን
     - ለ. ዓላማ
3. **መዋቅርና ይዘት**
   - 3.1 የመሲሁ መምጣት አዋጅ
   - 3.2 የመሲሁ ኃይል
     - ሀ. መግቢያ
     - ለ. በቅፍርናሆም አቅራቢ
     - ሐ. የገሊላ አውራጃ
     - መ. ከገሊላ ባሻገር
   - 3.3 ስለ መሲሁ የሐዋርያት ማረጋገጫ
   - 3.4 መከራን የሚቀበለው መሲህ
     - ሀ. ዝግጅት
     - ለ. ፍልሚያ
     - ሐ. ልምድ
   - 3.5 የመሲሁ ድል
4. **ዐቢይ መሪ ሃሳቦች**
   - 4.1 መከራን የተቀበለው አገልጋይ
     - ሀ. የአይሁድ ግምት
     - ለ. የኢየሱስ አገልግሎት
     - ሐ. ተገቢ ምላሽ
   - 4.2 ድል ነሺው ንጉሥ
     - ሀ. የመንግሥቱ መታወጅ
     - ለ. የተገለጠው ኃይልና ሥልጣን
     - ሐ. ጠላቶችን ድል ማድረግ
5. **ማጠቃለያ**

### መግቢያ

በሺዎች የሚቆጠሩ ክርስቲያኖች ክርስቶስን በመከተላቸው ብቻ በየዕለቱ በልዩ ልዩ መከራዎች ውስጥ ያልፋሉ። በየዕለቱም፣ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ አማኞች ንብረታቸው ይዘረፋል፤ መሪዎቻቸውም ይደበደባሉ በወህኒም ይጣላሉ፤ ቤተሰቦቻቸው ይሰቃያሉ፣ ይታፈናሉ፣ አልፎም ይገደላሉ።

በመሠረቱ፣ አሁን እኛ የአዲስ ኪዳን ሁለተኛው ወንጌል ብለን የምንጠራውን ወንጌል ማርቆስ በሚጽፍበት ወቅት የክርስቲያኖችን ስደት በልቡናው ውስጥ አድርጎ ነበር። ቀደምቲቱ የክርስቲያኖች ቤተ ክርስቲያን በብዙ መንገዶች በመከራ ውስጥ አልፋለች። ጉዳዩ ግን አማኞቹ የመከራቸውን ወሳኝነት እንዴት ተረዱት? የሚለው ነው። ስለ ችግሮቻቸው የኢየሱስ ምሳሌነት ምን አስተምሯቸዋል? የቀደሙትን ክርስቲኖች እምነት በሚያጠነክር፣ በሚያበረታታና እንዲፀኑ በሚያስችላቸው መንገድ ስለ ኢየሱስ ታሪክ በማውሳት ማርቆስ እነዚህን ለመሳሰሉት ጥያቄዎች ምለሽ ይሰጣል።

ወንጌላት ከተሰኘው ተከታታይ ትምህርታችን ይህ ሦስተኛውና **"የማርቆስ ወንጌል"** ብለን የሰየምነው ትምህርታችን ነው። በዚህ ትምህርት፣ ማርቆስ ስለ ኢየሱስ ሕይወት የጻፈውን በመመልከት በዘመነኛው ሕይወታችን ትምህርቶቹን ተግባራዊ እናደርጋቸዋለን።

የማርቆስ ወንጌል ጥናታችን በሦስት ዋና ክፍሎች የተከፈለ ነው። በመጀመሪያ፣ የማርቆስን ወንጌል ዳራ እንመለከታለን። ሁለተኛ፣ አወቃቀሩንና ይዘቱን እንዳስሳለን። ሦስተኛ ደግሞ፣ ዋና ዋና መሪ ርዕሶቹን እንመለከታለን። በማርቆስ ወንጌል ዳራ እንጀምር።

# ዳራ

የማርቆስን ወንጌል ዳራ ራሱን ጸሐፊውን የማርቆስ፣ ቀደምት ተደራሲያኑን እና የጻፈበትን ወቅትና ሁኔታዎች በመቃኘት እንዳስሰዋለን። አስቀድመን የማርቆስን ወንጌል ጸሐፊ እንመልከት።

## ጸሐፊ

የማርቆስን ወንጌል ጸሐፊነት በሁለት ክፍሎች እንመለከተዋለን። በመጀመሪያ፣ ስለ እርሱ ጸሐፊነት ትውፊታዊውን አመለካት እንቃኛለን። ሁለተኛ ደግሞ፣ የጸሐፊውን የግል ታሪክ እንመረምራለን። እስኪ አስቀድመን በዚህ ወንጌል ጸሐፊነት ትውፊታዊ አመለካከት እንጀምር።

### ትውፊታዊ አመለካከት

> ***የማርቆስ ወንጌል በማርቆስ እንደተጻፈ የቀደምት ቤተክርስቲያን ትውፊት በአንድ ድምፅ ያረጋግጣል። አዲስ ኪዳንን ስንመለከት፣ ዮሐንስ ማርቆስ የበርናባስ የአጎት ልጅ ነው። በሐዋርያት ሥራ እንደምናነበበው በመጀመሪያው ሚሲዮናዊ ጉዞ ከጳውሎስና ከበርናባስ ጋር አብሮ ነበር። እናቱም ቀደምት ሐዋርያት የሚሰበሰቡበት ቤት በኢየሩሳሌም ያላት እንደሆነ ተገልጧል። ጴጥሮስም በአንዱ ደብዳቤው ዮሐንስ ማርቆስን ልጅ ብሎ ጠቅሶታል። ዮሐንስ ማርቆስ በሮሜ ዙሪያ ጴጥሮስን ይከተል እንደነበረና ትምህርቶቹንም በትክክል እንደ ጻፈ ፓፒያስ ተናግሯል። (ዶ/ር ሮበርት ሉመር)***

ከቀደምት ክርስቲያን ጸሐፊዎች መካከል ሁለተኛውን ወንጌል ማርቆስ እንደጻፈ የተናገረው ፓፒያስ ነው፡፡ ፓፒያስ በሁለተኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ላይ የኖረ ሲሆን፣ በ130 ዓ.ም. በትንሿ እሲያ ፓፓስ የነበረ ሰው ነው፡፡

ስለ ፓፒያስ አመለካከት የምናውቀው ታዋቂ የሆነው የቤተክርስቲያን ታሪክ አዋቂ ከኢዮሲበስ በ325 ዓ.ም. ከጻፈው ነው፡፡ *Ecclesiastical History* በተሰኘው 3ኛ መጽሐፉ ምእራፍ 39 ክፍል 15 ውስጥ፣ ይህንን ጥቅስ ከፓፒያስ አጣቅሶልናል፡፡

> ***የጴጥሮስ አስተርጓሚ የሆነው ማርቆስ፣ ምንም እንኳን ቅደም ተከተልን የጠበቀ ባይሆንም እንኳን፣ ክርስቶስ የተናገራቸውንና ያደረጋቸውን ሁሉ በትክክል ጽፏቸዋል፡፡ እርሱ በቀጥታ ከጌታ ባይሰማም ወይም ባይከተለውም፣ በኋላ ግን፣ እንደተናገርሁት፣ ጴጥሮስን ይከተል ነበርና የአድማጮቹን መሻት ለማሟላት የእርሱን ትምህርቶች ወሰዷል፡፡***

እንደ ፓፒያስ አገላለጽ፣ የማርቆስ ወንጌል በጽናት የተመሠረተው በሐዋርያው ጴጥሮስ ትምህርቶች ላይ ነበር፡፡ ማርቆስ የኢሱስ አገልግሎት የዐይን ምስክር አልነበረም፣ ሆኖም ጴጥሮስ ከኢየሱስ ያየውንና የሰማውን መዝግቦልናል፡፡

በቀደመችው ቤተክርስቲያን የነበሩ ሌሎች ጸሐፍትም ይህንን ወንጌል ማርቆስ ጽፎታል የሚለውን ትውፊት ያረጋግጣሉ፡፡ ለምሳሌ፣ በ170 ዓ.ም. አካባቢ የተጻፈው የሁለተኛው ወንጌል *Anti-Marcionite Prologue* ፣ የማርቆስን ጸሐፊነት ያረጋግጣል፡፡ የቤተክርስቲያን አባት የሆነው ኢራኒየስም ይህንን አመለካከት ያጸናዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ፣ ቀደምቱ የግሪክ ቅጂዎች “ማርቆስ እንደ ጻፈው” የሚል ርዕስ ይሰጡታል፡፡

ሁለተኛውን ወንጌል ማርቆስ ጽፎታል የሚለው ማረጋገጫ በቀደመችው ቤተክርስቲያን ውስጥ የተሰፋፋ ነበር፡፡ እንዲያውም፣ ከቀደመችው ቤተክርስቲያን ስለ እርሱ ጸሐፊነት ይህ ነው የሚባል ሙግት ተመዝግቦ አናገኝም፡፡ ምንም እንኳን በቅርብ ምዕተ ዓመታት አንዳንድ ምሁራን ይህንን ተውፊታዊ አመለካከት ሊክዱ ቢሞክሩም፣ የማርቆስን ጸሐፊነት የሚያረጋግጠውን ቀደምት ምስክርነት ማስተባበል አልቻሉም፣ ወይም ማርቆስን ከጸሐፊነቱ ሊያገልለው የሚችል ፍንጭ በራሱ በወንጌሉም ውስጥ እንኳን ማመልከት አልቻሉም፡፡ በእነዚህ ምክንያቶች፣ የዘመኑ ክርስቲያኖች ይህንን ወንጌል ማርቆስ እንደጻፈው በልበ ሙሉነት ሊያረጋግጡ ይችላሉ፡፡

ይህንን ወንጌል ማርቆስ ጽፎታል የሚለውን ትውፊታዊ አመለካት ካረጋገጥን፣ አሁን ደግሞ የእርሱን ወንጌል የበለጠ መረዳት እንችል ዘንድ የግል ታሪኩን እንመልከት፡፡

## የግል ታሪክ

እንደ ሐዋርያት ሥራ 12፥12 አገላለፅ፣ ማርቆስ ማርያም የምትባል በኢየሩሳሌም ነዋሪ የሆነች ሴት ልጅ ነበር፡፡ ቤቷም ጴጥሮስ በእስር ላይ በነበረ ወቅት በኢየሩሳሌም ይኖሩ የነበሩ ጥቂት ክርስቲያኖች ለጴጥሮስ ይፀልዩበት የነበረው ቤት ነበር፡፡ ስለዚህ፣ ማርቆስ ከጴጥሮስና ከሌሎች ሐዋርያት ጋር የነበረው ግንኙነት የጀመረው ገና በጠዋቱ ነበር ማለት ነው፡፡

ማርቆስ በቆላስይስ 4፥10 እንደጠቀሰውም፣ ማርቆስ የበርናባስም የአጎቱ ልጅ ነበር፡፡ በርናባስና ጳውሎስ ባደረጉት የመጀመሪያ ሚሲዮናዊ ጉዞ ወቅትም ረድቷቸውም ነበር፡፡ ከሐዋርያት ሥራ 13፥13 እንደምንረዳው ግን፣ ማርቆስ ጉዞውን አቋርጦ ተለይቷቸው ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሶ ነበር፡፡

በውጤቱም፣ በሁለተኛው ሚሲዮናዊ ጉዞው ወቅት ፓውሎስ ማርቆስን ተሳታፊ ማድረግን ተቃውሞ ነበር፡፡ በሐዋርያት ሥራ 15፥36-41 እንደምናነብበው፣ በጉዳዩ ፓውሎስና በርናባስ ተለያይተዋል፡፡ ስለዚህም፣ በርናባስ በቆጵሮስ ለሚያደርገው አገልግሎት ማርቆስን ይዞ ሲሄድ፣ ጳውሎስን ግን በበርናባስ ምትክ ሲላስን ይዞ ሄደ፡፡

እንደ ቆላስይስ 4፥10 አገላለጥ፣ የኋላ ኋላ ግን ማርቆስ ጳውሎስ የሚተማመንበት ሰው እንደሆነ እናያለን እንዲያውም ከጳውሎስ እስሮች በአንዱ አብሮት ነበር፡፡

ቆየት ብሎም፣ ጴጥሮስ በሮም ሲያገለግል፣ ማርቆስ አግዞት ነበር፡፡ እንዲያውም፣ ጴጥሮስ በ1ኛ ጴጥሮስ 5፥13 ውስጥ "**ልጄ**" ብሎ ሲጠራው በመካከላቸው የጠበቀ ግንኙነት መኖሩን እናስተውላለን፡፡ ምናልባትም ጴጥሮስ በማርቆስ ወንጌል ተመዝግቦ በምናየው መንገድ ስለ ኢየሱስ ምድራዊ አገልግሎት ማርቆስን በውል ያስተማረው በዚህን ወቅት ሊሆን ይችላል፡፡

> ***ማርቆስ፣ በሙሉ ስሙ ዮሐንስ ማርቆስ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አሰደናቂ ገፀ-ባህርይ ነው፡፡ ለጥቂት ጊዜያት ብቻ በውስን ነገሮች ላይ ተገልጦ የምናየው ሰው ነው፡፡ እናቱ ማርያም ትባላለች፡፡ እናቱ በኢየሩሳሌም ቤት ነበራት፣ ይህንንም ያወቅነው፣ ቤተክርስቲያን አንዳንድ ጊዜ በዚያ ቤት ትሰበሰብ ነበር፡፡ የሐዋርያው ጳውሎስ ሚሲዮናዊ ባልደረባ የነበረው የበርናባስ የአጎት ልጅ ነበር፡፡ በመጀመሪያው ሚሲዮናዊ ጉዟቸው ወቅት ከጳውሎስና ከበርናባስ ጋር ተጉዟል፡፡ የቤተክርስቲያን ታሪክ እንደሚነግረንም ከጴጥሮስም ጋር የቀረበ ግንኙነት ነበረው፡፡ እንዲያውም፣ የቤተክርስቲያን ትውፊት እንደሚነግረን ማርቆስ፣ ወንጌሉ፣ የጴጥሮስ መልእክት ሰብሰቦች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ስለዚህ አንዳንድ ሰዎች፣ "መልካም፣ ማርቆስ ማነው?ሐዋርያ አልነበረም፡፡" ይላሉ፡፡ በእርግጥም እርሱ ሐዋርያ አልነበረም፣ ግን እስኪ ማስረጃዎቹን ተመልከቱ፤ አስገራሚ ማስረጃዎች ናቸው፡፡ በወቅቱ ወጣት የነበረ ቢሆንም፣ በብዙ መጠን በእርግጠኝነት ኢየሱስን ዐይቶታል ያውቀዋልም፡፡ ስለዚህም እርሱ የኢየሱስ የዐይን ምስክርም ነበር፣ በጣም በእርግጥም የትንሣኤውም የዐይን ምስክር ነበር፡፡ ለመሆኑ ሜንቶሮቹ እነማን ነበሩ? ሁለቱ ሜንቶሮቹ የአህዛብ ሐዋርያ የሆነው ጳውሎስ እና የዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ወኪል የነበረው፣ ጴጥሮስ ናቸው፡፡ ስለዚህ፣ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ለመጻፍ ብቁ ነበርን? ያለጥርጥር ብቁ ነበር፡፡ (ዶ/ር ማርክ ስትራውስ)***

ማርቆስ የወንጌሉ ጸሐፊ ስለመሆኑ ተነጋግረናል፣ አሁን ደግሞ የማርቆስን ቀደምት ተደራሲያን ማንነት መዳሰስ ይገባናል፡፡

## ቀደምት ተደራሲያን

የጥንቷ ቤተክርስቲያን ምስክርነትና የማርቆስ ወንጌል የተለያዩ ዝርዝሮች የሚያመለክቱት በጣሊያን ወደ ሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት ሲሆን፣ በተለይም በሮም ከተማ ያሉት፣ እንደ ማርቆስ ቀደምት ተደራሲያን ይታወቃሉ፡፡

የጥንቷን ቤተክርስቲያን ምስክርነትና የማርቆስን ወንጌል የራሱን ዝርዝሮች ስንመለከት ማርቆስ የጻፈው በኢጣሊያ በተለይም በሮም ለሚገኙ ጽፏል የሚለውን ሃሳብ እንመረምራለን፡፡ አስቀድመን ወደ ጥንቷ ቤተክርስቲያን ምስክርነት እንመለስ፡፡

## የጥንቷ ቤተክርስቲያን ምስክርነት

ቀደም ብለን የጠቀስናቸው ሦስቱ ጥንታዊ ምስክሮች ማለትም ፓፒያስ (በ130 ዓ.ም. አካባ የጻፈው)፣ የ *Anti-Marcionite Prologue* (በ170 ዓ.ም. አካባቢ የተፃፈ) እና ኢራኒየስ (በ177 ዓ.ም. አካባቢ የጻፈ) ሁሉም እንደመዘገቡት ወንጌሉን የጻፈው በኢጣሊያ ነው፣ አንዳንዶቹም በተለይ የሮምን ከተማ ይጠቅሳሉ፡፡ ከዚያም ባሻገር፣ ማርቆስ ወንጌሉን ወደየትኞቹም ሌሎች ከተሞች ስለመላኩ አንዳቸውም አልተናገሩም፡፡ ይህ የሚያመለክተው ማርቆስ የጻፈው ይኖርባት ለነበረው አጥቢያ መሆኑን ነው፡፡ ይህ ድምዳሜም የሚጠናከረው በ1ኛ ጴጥሮስ 5፥13 ማርቆስ ከጴጥሮስ ጋር በሮም ያገለግል የነበረ መሆኑ በተገለጠበት ክፍል ነው፡፡

እርግጥ ነው፣ እንደ ሌሎቹ ወንጌላት፣ የማርቆስም ወንጌል በሁሉም ዘመናት በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ጥቅም ላይ እንዲውል የእግዚአብሔር ሃሳብ ነበር፡፡ ሆኖም የማርቆስን ወንጌል የጻፈው በእርሱ ዘመን ይኖሩ ለነበሩ የሮም ክርስቲያኖች ከነበረው ጥልቅ ግድ የመሰኘት ስሜት እንደነበረ ስናውቅ የማርቆስን ወንጌል በዚያ አንጻር ለመፍታት ይበልጡኑ ዝግጁ እንሆናለን፡፡

ከጥንታዊቷ ቤተክርስቲያን ምስክሮች በተጨማሪም፣ የማርቆስ ወንጌል በርካታ ዝርዝሮች በኢጣሊያ በተለይም ደግሞ በሮም ላሉ ቤተክርስቲያናት እንደጻፈው ያመለክታሉ፡፡ ለኢጣሊያና ለሮም ቤተክርስቲያናት ጽፎታል የሚለውን ሃሳብ የሚያፀኑ አራት የማርቆስ ወንጌል ዝርዝሮችን እንጠቅሳለን፡፡

## የወንጌሉ ዝርዝሮች

በመጀመሪያ፣ በበርካታ ጊዜያት፣ ማርቆስ የፓለስቲኒያን ወግ ለተደራሲያኑ ይጠቅሳል፡ ለምሳሌ፣ በማርቆስ 7፥3-4 ውስጥ፣ የፈሪሳውያንን እጅ የመታጠብ ልምምድ ማርቆስ ያብራራል፡፡ ይህንን የመሰለው ማብራሪያ የሚያመለክተው የማርቆስ ተደራሲያን ከፓለስታይን ውጪ የሚኖሩ በርካታ ቁጥር ያላቸው አህዛብ የተካተቱበት መሆኑን ነው፡፡

ሁለተኛውና የማርቆስ ተደራሲያን ኢጣሊያኖችና ሮማውያን ናቸው ከሚለው ጋር የሚስማማው ዝርዝር ማርቆስ የአራማይስጥ መግለጫዎችን ማብራራቱ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ በማርቆስ 3፥17 ውስጥ ለያዕቆብና ለዮሐንስ የተሰጣቸውን ስም ያብራራበትን አድምጡ፡

> **የዘብዴዎስንም ልጅ ያዕቆብን የያዕቆብንም ወንድም ዮሐንስን ቦአኔርጌስ ብሎ ሰየማቸው፥ የነጎድጓድ ልጆች ማለት ነው፤ (ማርቆስ 3፥17)**

ማርቆስ በ5፥41፣ 7፥34 እና 15፥22፣34 ውስጥም ተመሳሳይ ማብራሪያ ይሰጣል፡፡ አራማይስጥ ተናጋሪ የሆኑት ፓለስቲኒያውያን እነዚህ ማብራሪያዎች አያስፈልጓቸውም፣ ከፓለስቲኒያ ውጪ የሚኖሩት አይሁድ እንኳን ከምኩራቦቻቸው የተነሳ ለአራማይስጥና ለዕብራይስጥ ቅርብ ናቸው፡፡ እንግዲያው ይህ ዝርዝር እንደሚያመለክተን ማርቆስ የጻፈው ከፓለስታይን ውጪ ለሚኖሩ አህዛብ መሆኑን ነው፡፡

ተደራሲያኑ የኢጣሊያና የሮም ሰዎች መሆናቸውን በበለጠ ግልጽነት የሚሳየን ሦስተኛው ዝርዝር ማርቆስ ከሌሎቹ ወንጌላት ይልቅ የላቲን ቃላትን የተጠቀመ መሆኑ ሲሆን፣ ከተደራሲያኑ አብዛኛውን ቁጥር የሚይዙት የላቲንን ቋንቋ የሚረዱ መሆናቸውን ነው፡፡

በመጀመሪያው ምዕተ ዓመት፣ በሜድትራኒያኑ ዓለም ውስጥ ላቲን በስፋት አይነገርም ነበር፡፡ በቀደምትነት የሮም አገዛዝ ዕምብርት በነበረችው በኢጣሊያ የተገደበ ነበር፡፡ ስለዚህ፣ ጳውሎስ ቢያንስ 15 ጊዜያት የላቲን ቃላትን መጠቀሙ ወሳኝነት አለው፡፡ ለምሳሌ፣ በማርቆስ 12፥42 ውስጥ፣ ሌፕታ (እኛ ቤሳ የምንለው) የሚለውን የላቲን ቃል፣ አነስተኛ የሆነን የነሃስ ሳንቲም ለመግለጥ ተጠቅሞበታል፡፡ ፊደላቱን በግሪክኛው አጣጣል ቢጽፋቸውም፣ ቃሉ ራሱ ግን የላቲን ነበር እና የላቲን ቋንቋ ለማይናገሩ ሰዎች ሊገባ የሚችል አይሆንም፡፡

ማርቆስ ለኢጣሊያ በተለይም ለሮም ቤተክርስቲያን ነው የጻፈው የሚለውን ሃሳብ አሳማኝ የሚያደርገው አራተኛው ዝርዝር ማርቆስ ሩፎስ የሚባልን ሰው መጥቀሱ ነው፡፡

በማርቆስ 15፥21 ውስጥ፣ የኢየሱስን መስቀል እስከ ጎልጎታ የተሸከመው ሰው የሩፎስ እና የእስክንድር አባት መሆኑን እንረዳለን፡፡ ሁለቱ ሰዎች በማርቆስ ወንጌል ውስጥ ምንም ሚና የላቸውም፡፡ ታዲያ ማርቆስ ለምን ጠቀሳቸው? ከተመረጡ መግለጫዎች አንዱ በማርቆስ ተደራሲያን በውል የሚታወቅ ወይም የማርቆስ ተደራሲ ነበር የሚለው ነው፡፡ እንዲያውም፣ ሩፎስ የተሰኘው ሰው በሮሜ 16፥13 ውስጥ የሮሜ ቤተክርስቲያን አባል መሆኑ ተጠቅሷል፡፡ ማርቆስ የጠቀሰው ይህ ሩፎስ የተሰኘው ሰው ያው ሰው ከሆነ፣ ማርቆስ ለሮሜ ቤተክርስቲያን ጽፏል የሚለውን እንድምታ ያጸናዋል፡፡

ከእነዚህ ዝርዝሮች አንዳቸውም ለብቻቸው ሮም የማርቆስ አድራሻ መሆኑን አያረጋግጡም፡፡ ሆኖም ድምር ማስረጃነታቸው ግን የጥንቷን ቤተክርስቲያን ጠንካራ ምስክርነት ያረጋግጥልናል፡፡ በዚህ ትምህርት ወደ ኋላ ላይ እንደምንመለከተው፣ የሮሜ ተደራሲያንን በልቡናችን ይዘን የማርቆስን ወንጌል ማንበባችን የማርቆስን ልዩ አፅንዖት እንድንረዳ እና በዘመናዊቷ ቤተክርስቲያን ሕይወት ተግባራዊ እንድናደርግ ያስችለናል፡፡

የዚህን ወንጌል ጸሐፊና ቀደምት ተደራሲያን በልቡናችን ይዘን፣ የማርቆስን ወንጌል ሦስተኛ ገፅታ እንመረምራለን፡፡ ያም የጥንቅሩ ወቅት ወይም ሁኔታ ነው፡፡

## ወቅት

የማርቆስን ወንጌል ሁኔታ ሁለት ገፅታዎች እንመረምራለን፡፡ በመጀመሪያ፣ ማርቆስ መቼ ጻፈ የሚለውን እንዳስሳለን፡፡ ሁለተኛ ደግሞ፣ የጻፈበትን ዓላማ እንመረምራለን፡፡ የማርቆስ ወንጌል በተጻፈበት ወቅት እንጀምር፡፡

### ቀን

የማርቆስ ወንጌል የተጠናቀረበትን ቁርጥ ያለ ቀን በእርግጠንነት ማስቀመጥ አይቻልም፡፡ በጥቅሉ ግን፣ ማስረጃዎቹ በመጀመሪያው ምዕተ-ዓመት መካከል ወይም ማክተሚያ አካባቢ ላይ እንደሚሆን ይጠቁማሉ፡፡

ኢራኒየስን የመሳሰሉ የጥንት ምስክሮች እና ስለ ማርቆስ ወንጌል የተጻፈው *Anti-Marcionite Prologue* ማርቆስ ወንጌሉን የጻፈው ከጴጥሮስ ሞት በኋላ መሆኑን ይናገራሉ፡፡ ጴጥሮስ የተገደለው በ64

ዓ.ም. የሮምን መቃጠል ተከትሎ ቤተክርስቲያን በሮሙ ንጉሥ በኔሮ ስቃይ ውስጥ በገባችበት መከራ ወቅት ሊሆን እንደሚችል ይታሰባል። ማርቆስ ሥራውን የጀመረው ጴጥሮስ በሕይወት እንዳለ መሆኑን ቢያመለክትም፣ ማርቆስ ሥራውን ሳያጠናቅቅ በፊት ጴጥሮስ ሞቶ ሊሆን ይችላል የሚለውን እሳቤ ቁርጥ አድርጎ ማስቀመጥ አልቻለም። ስለዚህ፣ ማርቆስ ወንጌሉን ጽፏል ተብሎ የሚታሰብበት ቀደምት ጊዜ ጴጥሮስ በሞተበት በ64 ዓ.ም. አካባቢ ሊሆን እንደሚችል መቀበሉ ምክንያታዊ ነው።

ማርቆስ ጻፈበት የሚባለውን ዘግየት ያለ ጊዜ መለየት አስቸጋሪ ነው። ቀደም ባለው ትምህርት እንዳየነው፣ የማርቆስ ወንጌል የመጀመሪያው ወንጌል ነው እናም ማቴዎስና ማርቆስ ወንጌሎቻቸውን ሲጽፉ የማርቆስን ወንጌል እንደ ማገናዘቢያ ተጠቅመውበታል ብለው በርካታ ምሁራን ያምናሉ። ከእነዚህ ሦስት ወንጌላት አንዳቸውም በ70ዓ.ም. የተከናወነውን የኢየሩሳሌምንና የመቅደሷን መፍረስ እስካልጠቀሱ ድረስ፣ ማቴዎስ፣ ማርቆስና ሉቃስ ሁሉም ከዚያን በፊት እንደተጻፉ በርካታ ምሁራን ይስማማሉ። እናም ማቴዎስና ሉቃስ የራሳቸውን ሥራ ከማጠናቀቃቸው በፊት የማርቆስን ወንጌል ከተቀበሉና ከተጠቀሙበት፣ ማርቆስ ወንጌሉን ያጠናቀቀው ከ70 ዓ.ም ቀደም ብሎ መሆኑን መገመት አስተማማኝ ነው። በእርግጠኝነት 69ዓ.ም. ሲሆን፣ ምናልባትም በ67 ዓ.ም. ጅማሬ ላይ ሊሆን ይችላል፣ ይህም ማቴዎስና ማርቆስ ወንጌሎቻቸውን ከመጻፋቸው በፊት ከማርቆስ ወንጌል ጋር ለመተዋወቅ ሰፋ ያለ ጊዜ ይሰጣቸዋል።

የማርቆስ ወንጌል የተጻፈበትን ጊዜ በልቡናችን ይዘን፣ የጻፈበትን ዓላማ እንመልከት።

**ዓላማ**

በአንድ በኩል፣ ማርቆስና የተቀሩት ሁሉም ወንጌላት አንድ የጋራ ዓላማ አላቸው ያም የኢየሱስን እውነተኛ ሕይወትና ትምህርቶች ጠብቆ ማቆየት ነው። ከ50 ዓ.ም. ጀምሮ በቀጣዮቹ ዓመታት የኢሱስ ሕይወት፣ ሞትና ትንሣኤ ምስክሮች የሆኑት ሐዋርያት በሚጨምር መጠን እየሞቱ ነበር። ስለዚህም፣ ምስክርነታቸውን ጠብቆ የማቆቱ ፍላጎት እያደር ይጨምር ነበር። ኢዮሲበስ እና ሌሎች ቀደምት የቤተክርስቲን ፀሐፍት እንደጠቀሱት፣ ስለ ኢየሱስ አገልግሎት ጴጥሮስ የመዘገበውን ጠብቆ ማቆየት የማርቆስ ዓላማ አካል ነው።

የማርቆስ ዓላማ ይህንን ታሪክ ጠብቆ ማቆየት ብቻ አልነበረም። እንደ ሌሎቹ የወንጌላት ጸሐፊዎች ሁሉ፣ ማርቆስም አንባቢዎቹ ስለ ኢየሱስ እንዲያውቁ ብቻ አይፈልግም። ከኢየሱስ ሕይወት ዛሬ እነርሱ ተግባራዊ ሊያደርጉ የሚገባቸውንም ትምህርት እንዲያገኙም ይፈልግ ነበር። ግን ሕይወታቸው ምን ይመስል ነበር?

> ***በ 60ዎቹ ዓ.ም. በሮም ውስጥ መኖር ለክርስቲያኖች በጣም ፈታኝ ነበር። እስከዚያን ዘመን ድረስ፣ በሮም ሕግ ውስጥ፣ አይሁድ ከሆንህ የአንድ የታወቀ ሃይማኖት አካል ነህ ማለት ነው፤ ያም religio licita, የተፈቀደ ሃይማኖት እንደማለት ነው። እናም አይሁድ ክርስቲያኖች ብዙ መከራ የለባቸውም ምክንያቱም ሮማውያን "ያው፣ የጁዳይዝም አካል ናቸው" ብለው ያስቡ ስለነበር ነው። ግን የሮም ባለሥልጣናት "አሃ፣ ይህ አዲስ ሃይማኖት ነው፣ አይሁድ ያልሆኑትን፣ አህዛብንም የሚጨምር ይመስላልና ከጁዳይዝም ልዩ ነው?" ብለው መረዳት ሲጀምሩ ምን የሚሆን ይመስላችኋል? በድንገት ጉዳዩ የሮሜ ባለሥልጣናትን ትኩረት ሳበ፣ እናም ከዚያ በኋላ የተፈቀደና የማያሰጋ ሃይማኖት የመሆኑ ነገር አበቃ። እንግዲህ፣ መከሰት የጀመረው ይህ ነገር ነው፣ ወይም***

*በ60ዎቹ ውስጥ ነገሩ እየተለየ መጣ፡፡ በ59 ዓ.ም. ኔሮ በጥቂቱ ተበሳጨ፣ ከዚያም የንግሥናው አምስት አመታት በመጠኑ ደህና ነበሩ፣ ከዚያ በኋላ እስከሞተበት 68ዓ.ም. ድረስ፣ ሊገመት የማይችል ሰው እየሆነ መጣ፡፡ ከዚያም፣ ጳውሎስ በ60ዓ.ም ሮም ሲደርስ እና ለክርስቶስ ለመሞት ፈቃደኛ መሆኑን ደግሞም ይህ አዲስ ሃይማኖት ለሁሉም ሰው፣ ንጉሠ ነገሥት ኔሮን ጨምሮ መሆኑን አሳየ፡፡ ከዚያም ኔሮ ጉዳዩን ሲጋፈጠው፣ እርሱ የማይወድደው ሃይማኖት ሆኖ አገኘው፡፡ በሥልጣን ላይ ያለሁት እኔ ነኝ፣ እነዚህ ክርስቲያኖች ግን "ኢየሱስ ጌታ ነው" እያሉ ያውጃሉ፡፡ እናም፣ ጁላይ 18 ቀን 64ዓ.ም. ሮም በእሳት ስትጋይ፣ ተወቃሹ ኔሮ ሆነ፤ እርሱ ግን ወቀሳውን ወደ አዲሱ ቡድን፣ ክርስቲያን ተብሎ ወደሚጠራው ወገን፣ አላከከው እናም ምን ያህል አሰቃቂ እንደነበር የሰማነው እርሱን ነው፡፡ (ዶ/ር ፒተር ዎከር)*

ማርቆስ በጻፈባቸው ዓመታት፣ በሮም የምትገኘው ቤተክርስቲያን በሮማው ንጉሥ ኔሮ በከባድ መከራ ውስጥ ነበረች፡፡ ኔሮ የገዛው ከ54 እስከ 68 ዓ.ም. ነበር፡፡ ሮም በ64 ዓ.ም. የመቃጠሏን ተጠያቂነት በክርስቲያኖች ላይ በማላከክ የለየለት ሰው ስለነበር፣ በአሰቃቂ ሁኔታ ቀጣቸው፡፡

*በኔሮ አገዛዝ ዘመን፣ ሮሜ ክርስቲያኖችን በአሰቃቂ ሁኔታ መከራ አድርሳባቸው ነበር፡፡ በመጀመሪያ፣ ሮም እንደ ሪፐብሊክ ተመሰረተች፡፡ በኋላ ግን፣ ከዩሊየስ ቄሳር ግድያ በኋላ፣ አውግስቶስ ጦሩን በመምራት የሮምን ከተማ ወረረ ምክር ቤቱንም በተነው፡፡ ስለዚህም፣ የሮሜ ሪፐብሊክ፣ ወደ ሮም ግዛትነት ተለወጠች አውግስቶስም የመጀመሪያ ንጉሷ ሆነ፡፡ የሮሜ የጭካኔ ታሪክ እዚያ ጋ ይጀምራል፡፡ በመሠረቱ፣ ክርስቲያኖችን ከማሳደድ አንፃር ኔሮ ከሁሉ የሚከፋው አልነበረም፡፡ ታሪክ እንደሚነግረን፣ ሌሎቹም ነገሥታት እጅግ በአሰቃቂ ሁኔታ ክርስትናን አጥቅተውታል እናም በርካታ ክርስቲያኖች ተሰቃይተዋል፣ በመስቀል ላይ በሚስማር እየተቸነከሩ ሞተዋል ወይም በእሳት ተቃጥለው ሞተዋል፡፡ በቀደመችው ቤተክርስቲያን በርካታ ሰማዕታት የነበሩ ሲሆን በሞታቸውም የእግዚአብሔር ምህረትና ጽድቅ ምስክሮች ሆነዋል፡፡ (ዶ/ር ስቴፈን ቻን)*

በዚህ ዘመን በሮም ውስጥና በአቅራቢያዋ ለሚኖሩ ክርስቲያኖች ሕይወት በብዙ መንገዶች ፈታኝ ነበረች፡፡ እናም እንደምንመለከተው፣ ማርቆስ ወንጌሉን የቀረፀው ላሉበት ሁኔታ አገልግሎት ለመስጠት ነበር፡፡ የማርቆስን ጽሑፍ ዓላማ የምንገልጥባቸው በርካታ መንገዶች ቢኖሩም፣ በዚህ ትምህርት ግን ማርቆስ ወንጌሉን የጻፈው በሮም ውስጥ እተሰደዱ የነበሩ ክርስቲያኖችን ለማበርታት ነበር በሚለው ሃሳብ ላይ እናተኩራለን፡፡

የሮሜ ክርስቲያኖች ስለ ክርስቶስ በምንም ዓይነት መከራና ችግር ውስጥ ቢያልፉም፣ ኢየሱስ ራሱ አስቀድሞ ያለፈባቸው መሆኑን የማርቆስ ወንጌል ግልፅ ያደርገዋል፡፡ በሮም ፍርድ ቤት ውስጥ ያለ ፍርድ ተከስሷል፡፡ በሮም ወታደሮች ተደብድቧል፡፡ በሮማውያን መስቀልም ላይ ተሰቅሏል፡፡ ግን በመከራው ሁሉ ኢየሱስ ድል አድራጊ ነበር፡፡ ማርቆስ ተደራሲያኑን ሊያስረግጥላቸው የሚፈልገውም፣ ኢየሱስን በእምነት ቢከተሉ፣ እነርሱም ድል አድራጊ እንደሚሆኑ ነው፡፡ አዎን ሊሰቃዩ ይችላሉ፡፡ መከራቸው ግን ልክ ለኢየሱስ እንደነበረው ሁሉ፣ ለእነርሱም የክብር መንገዳቸው ነው፡፡

የማርቆስን ወንጌል ዳራ ከተመለከትን፣ ወደ አወቃቀሩና ይዘቱ ደግሞ እንሸጋገር፡፡

# ውቅርና ይዘት

በዋናነት፣ የማርቆስ ወንጌል በአምስት ዐቢይ ክፍሎች ይከፈላል፡፡ በመጀመሪያ፣ ማርቆስ ወንጌሉን የሚከፍተው ስለ ኢየሱስ መሲህነት በ1፥1-13 በሚሰጠው አጭር አዋጅ ነው፡፡ ሁለተኛ፣ የመሲሁን ኃይል የሚገልጠው ሰፋ ያለው ከ 1፥14 - 8፥26 ያለው ትረካ ነው፡፡ ሦስተኛ፣ በ8፥27-30 የሚገኘው፣ አጭርና ሐዋርያት ስለ መሲሁ የሰጡትን ማረጋገጫ የሚያቀርበው መዘውር ነው፡፡ አራተኛ፣ ሌላኛውና የመሲሁን መከራ የሚናገረው ከ 8፥31 - 15፥47 የሚዘልቀው ረጅሙ ትረካ ነው፡፡ አምስተኛ ደግሞ፣ አጭሩና የመሲሁን ድል የሚዘግበው በ16፥1-8 ያለው ነው፡፡ እነዚህን የማርቆስ ክፍፍሎች በበለጠ ጥልቀት እንመለከታቸዋለን፣ በመሲሁ አዋጅ እንጀምራለን፡፡

## የመሲሁ መምጣት አዋጅ

በማርቆስ 1፥1 ውስጥ ወንጌሉ እንዴት እንደሚጀምር አድምጡ፡

*የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል መጀመሪያ። (ማር 1፥1)*

ማርቆስ ኢየሱስን "**ክርስቶስ**" ብሎ ሲጠቅሰው፣ መሲህ የሚለውን የእብራይስጥ ቃል ከሪክኛ ቅጂ ተጠቅሞ ነው፡፡ በተመሳሳይ፣ የእግዚአብሔር ልጅ የሚለው ቃል ኢየሱስ የእግዚአብሔር መሲህ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

በብሉይ ኪዳንና በዘመናችን የአይሁድ ነገረ-መለኮት፣ መሲሁ ከዳዊት ቤት ሊሆን የተገባው ሲሆን እርሱም የእሥራኤልን መንበረ ንግሥና የሚመልስ እና ምድራቱንም በምድር የእግዚአብሔር መንግሥተ እንድትሆን ያደርጋል፡፡

ይህ የመክፈቻ አዋጅ በማርቆስ 1፥2-11 የሚገኘውንና ኢየሱስ በዮሐንስ ስለ መጠመቁ የሚያወሳውን ታሪክ ያስከትላል፡፡ ኢየሱስ ተጠምቆ ሲያበቃ፣ መንፈስ ቅዱስ በኢየሱስ ላይ ይወርዳል፣ ኢየሱስ የእርሱ የተወደደ ልጅ መሆኑን የሚያውጀው የእግዚአብሔር አብ ድምፅ ከሰማይ ይሰማል፡፡ በዚህ መንገድ፣ መንፈሱና አብ ኢየሱስ ሲጠበቅ የነበረው መሲህ እንደሆነ አረጋግጠዋል፡፡

> **በኢየሱስ ዘመን የነበሩ አይሁድ ከመሲሁ መምጣት አንፃር ምን ያስቡ እንደነበር ማሰብ ያስገርማል፡፡ በእርግጥም፣ በርካታ የተለያዩ አመለካከቶች ነበሩ፡፡ ከሙት ባህር ጥቅልሎች የተገኙ አንዳንድ ማስረጃዎች እንደሚያሳዩት አንዳንዶች ሁለት መሲሆች ይመጣሉ ብለው ያስባሉ፣ ካህናዊ መሲህና ንጉሣዊ መሲህ፡፡ ዋነኛው ግን መሲሁ የዳዊት ልጅ ይሆንና ሮማውያንን አስወጥቶ ፖለቲካዊ ሰላምን ያመጣል፡፡ እኔ እንደማስበው የተደራጀው ሃይማኖት የሚያምነው መንግሥቱ የሚመጣው እስራኤል ህጉን የምትታዘዝ ከሆነ ነው፡፡ እነርሱ ኢየሱስን ይመለከቱ የነበረው እንደ እንቅፋት ነበር፣ በዚህም ረገድ ቢያንስ በእነርሱ አመለካከት ኢየሱስ ለህጉ መታዘዝን የሚያበረታታ ሳይሆን መተላለፍን የሚያበረታታአድርገው ቆጥረውታል፡፡ እርሱ እነርሱ የሚጠብቁትን የፖለቲካ መዘውር ይዞ አልመጣም፣ ከህጉም አንፃር፣ እነርሱ እንደሚጠብቁት አላደረገም፣ እናም፣ እኔ እንደማስበው እርሱ አሳፋሪ ሆነባቸው፡፡ በቀኑ መጨረሻም፣ ኢየሱስን በዘዳግም 13 መነፅር አዩት፣ ያም ምልክቶችን፣ ድንቅና ተዓምራትን የሚያደርግ ሀሰተኛ ነቢይ ስለሆነ ሞት ይገባዋል የሚል አመለካከት ያዙ፡፡** (ዶ/ር ቶማስ ሽሬነር)

ኢየሱስ ግን ብዙዎች የሚጠብቁት ዓይነት መሲህ አልነበረም፡፡ በጥቅሉ፣ የመጀመሪያው ምዕተ-ዓመት አይሁድ ያስቡ የነበረው መሲሁ በእስራኤል ውስጥ በመዝመት መንግሥቱን ይወርሳል ብለው ነበር፡፡ በማርቆስ 1፥12-13 ውስጥ፣ ኢየሱስ ከተጠመቀ በኋላ ወዲያውኑ፣ መንፈስ ቅዱስ በሰይጣን ይፈተን ዘንድ ወደ ምድረ በዳ እንደወሰደው እንረዳለን፡፡ በፍፃሜው ድል ይነሳል፡፡ በእግዚአብሔር ዕቅድ መሠረት ግን፣ የእርሱ የድል መንገድ ረጅም የመከራ ጎዳና ነበር፡፡

ኢየሱስ እንደ መሲህ መታወጁን አስከትሎ፣ በማርቆስ 1፥14 - 8፥26 ውስጥ የመሲሁን ኃይል ማርቆስ ይገልጥልናል፡፡

## የመሲሁ ኃይል

በዚህ የማርቆስ ወንጌል ትረካ ውስጥ፣ ኢየሱስ እንደ መሲህ ኃይሉንና ሥልጣኑን መግለጥ ይጀምራል፡፡ ብዙ ህዝብ ከዚህ አገልግሎት የሚገኙ በረከቶችን ለመመልከት ይሰበሰብ ነበር፣ ሆኖም የኢየሱስ ኃይል እርሱ ክርስቶስ መሆኑን እንደሚያረጋግጥ አላወቁም፡፡ በመሠረቱ፣ በዚህ ክፍል ውስጥ የትም ቦታ ማንም ሰው ክርስቶስ መሆኑን አልጠቀሰም፡፡ እንዲያውም ኢየሱስ ስለ ማንነቱ ዝምታን የመረጠ ሲሆን፣ ሌሎችም ምንም እንዳይናገሩ ያስጠነቅቅ ነበር፡፡

እርግጥ ነው፣ በማርቆስ የሮሜ ተደራሲያን መካከል የመጀመሪያዎቹ አንባቢዎች ክርስቲኖች ስለነበሩ፣ ኢየሱስ መሲህ መሆኑን ቀድሞውኑም ያውቃሉ፡፡ በዚህ የትረካ ክፍል ውስጥ ማርቆስ የተከተለው ስልት ግን በኢየሱስ ዙሪያ የነበረው ህዝብ፣ ይህ አስደናቂ ኃይል የሚገለጥበት ሰው ማን ነው፣ ምንስ ለማድረግ መጣ የሚለውን ግርታቸውን እነርሱም እንዲሰማቸው ያስችላቸዋል፡፡

እንደ አለመታደል ሆኖ ግን፣ ነገር ነቃሽ ምሁራን ግን ይህንን የኢየሱስን ዝምታ ኢየሱስ በአገልግሎቱ ጅማሬ ላይ ስለ መሲሃዊ አገልግሎቱ እውቀት እንዳልነበረው አመልካች ነው በማለት እንዲቆጥሩት አድርጓቸዋል፡፡ በማርቆስ 1፥11 ውስጥ እንደምናየው ግን፣ የኢየሱስን መሲሃዊ አገልግሎት እግዚአብሔር ያወጀው ገና ሲጠመቅ ነበር፡፡ በዚህ ብርሃን መሠረት፣ የኢየሱስ ዝምታ ስልት እንደ ነበር መረዳት ይቻላል፡፡ ኢየሱስ ሊፈፅም የመጣው አንድ ግብ ነበረው፣ በርካታ ሰዎች ካጀቡት ግን፣ ግቡ ሊሰናከል እንደሚችል ያውቅ ነበር፡፡

የመሲሁን ኃይል የሚገልጠው የማርቆስ ትረካ በአራት ክፍሎች ሊከፈል ይችላል፡፡ አንደኛ፣ ማርቆስ የአጠቃላዩን ትረካ ሁኔታ የሚገልጥልንን መግቢያ ይሰጠናል፡፡ ሁለተኛ፣ በቅፍርናሆም ከተማ ኢየሱስ በሰጠው አገልግሎቱ ላይ ያተኩራል፡፡ ሦስተኛ፣ የኢየሱስ አገልግሎት በተቀረው የገሊላ አውራጃ መስፋፋቱን ያብራራል፡፡ አራተኛ ደግሞ፣ በስተመጨረሻው ኢየሱስ ከገሊላ ባሻገር፣ እንዲያውም በቀደምትነት የአህዛብ ወደ ነበሩትም አካባቢዎች የሄደ መሆኑን ዘግቧል፡፡ እነዚህን ሦስት ክፍሎች፣ በማርቆስ 1፥14-15 በተጠቀሰው መግቢያ በመጀመር እንመለከታቸዋለን፡፡

### መግቢያ

በማርቆስ 1፥15 ማርቆስ የኢሱስን ስብከት ያጠቃለለበትን መንገድ አድምጡ፡

ዘመኑ ተፈጸመ የእግዚአብሔርም መንግሥት ቀርባለች ንስሐ ግቡ በወንጌልም እመኑ! (ማርቆስ 1፥15)፡፡

በገሊላ የኢየሱስ ማዕከላዊ ዓላማ ወንጌልን ወይም መልካሙን የምሥራች መስበክ፣ የእግዚአብሔርም መንግሥት መቅረቧን እና ንስሓ ለሚገቡና ለሚያምኑ በረከቷ የሚሰጥ መሆኑን ማወጅ መሆኑን ማርቆስ አመልክቷል፡፡

ማርቆስ ስለ መሲሁ ኃይል ባሰፈረው ዘገባው ያተኮረው በቅፍርናሆም ከተማ አቅራቢያ በመጀመር በገሊላ አውራጃ እና በአካባቢው በተሰጠው የኢየሱስ አገልግሎት ላይና ከዚያ አንስቶ በመስፋፋቱ ላይ ነበር፡፡ የማርቆስን ዘገባ ከሌሎቹ ወንጌላት ጋር ስናነፃፅረው፣ ኢየሱስ በሌሎች ስፍራዎች ያገለገለባቸውን ጊዜያት ማርቆስ የዘለላቸው ይመስላል፡፡ ይህም የሚያመለክተው የማርቆስ ግቡ ኢየሱስ በተጓዘባቸው ስፍራዎች ሁሉ ያከናወናቸውን ዝርዝሮች ከማውሳት ይልቅ በገሊላ አውራጃ ያደረጋቸውን እንቅስቃሴዎችና ስልቶችን መዘገብ እንደነበረ ነው፡፡

ከመግቢያው በኋላ፣ በማርቆስ 1፥16 - 3፥6 ኢየሱስ በገሊላ አውራጃ በምትገኘው በቅፍርናሆም የሰጠውን አገልግሎት ማርቆስ ይገልጣል፡፡

## በቅፍርናሆም አቅራቢያ

በማርቆስ 1፥16-20 ኢየሱስ የመጀመሪያዎቹን ደቀ መዛሙርት መምረጡን መዘገብ ይጀምራል፡፡ በዚህ ክፍል፣ ሰዎች ለኢየሱስ ምላሽ ይሰጡ የነበሩበት አንዱ መንገድ በፍፁም የመታዘዝ መንፈስ እንደነበር እናያለን፡፡ ኢየሱስ ተከተሉኝ አላቸው፣ እነርሱም ይሠሩ የነበሩትን ትተው የእርሱ ደቀመዛሙርት/ተከታዮች ሆኑ፡፡

ቀጥሎም፣ በማርቆስ 1፥21-34 ኢየሱስ በቅፍርናሆም በማስተማርና ተዓምራትን በማድረግ ወንጌልን አውጇል፡፡

በዚህ ወቅት የኢየሱስ ዝና በገሊላ ዙሪያ ተስፋፍቶ ነበር፣ ከዚያም በአገልግሎቱ ሁሉ ውስጥ እየቀጠለ ሄዶ ነበር፡፡ ዝናው እየወጣ በመሄዱ ምክንያት፣ ህዝቡ በኢየሱስ ዙሪያ መሰባሰብ ጀመረ፣ ይህም በተደጋጋሚ ወንጌልን የማወጁንና በተግባር የመግለጡን ሥራ እንቅፋት ይሆን ነበር፡፡ ስለዚህም፣ እርሱ መሲህ መሆኑን እንዳይናገሩ ሌሎችን ማዘዝ ጀመረ፡፡

በማርቆስ 1፥35-45 እንደምንመለከተው፣ ኢየሱስ ከቅፍርናሆም በመውጣት በአጎራባች መንደሮች ማስተማርና ተዓምራት ማድረጉን ቀጠለ፡፡ በከፊል ወገኑ ኢየሱስ ወደ አጎራባች መንደሮች የሄደው በማስተማርና ተዓምራትን በማድረግ ወንጌሉን ለማስፋፋት ነበር፡፡ ግን በተጨማሪም ይህንን ያደረገው በነፃነት ለማገልገል እንቅፋት ከሆነበት ከቅፍርናሆም ህዝብ ለማምለጥ ነበር፡፡ ቀደም ብሎ እንዳደረገውም፣ የሚያገኛቸው ሁሉ ስለ እርሱ ምንም እንዳይናገሩ ማዘዙን ቀጠለ፡፡

ቀጥሎም፣ በማርቆስ 2፥1 - 3፥6 እንደምናነብበው፣ ኢየሱስ ከአይሁድ መሪዎች ጋር ወደ ተጋጨበት ወደ ቅፍርናሆም መመለሱን ማርቆስ ይዘግብልናል፡፡

ይህኛው የማርቆስ ወንጌል ክፍል የሚያወሳው ኢየሱስ ኃጢአትን ይቅር ለማለት ስላለው ሥልጣን፣ ኃጢአተኞችን ለማገልገል ስላለው ጽድቅ እና ስለ ሰንበት ስለሚያስተምረው ትምህርት ነው፡፡ በተጨማሪ ግን እያደገ የመጣው ዝናው ስላስከተለበት ሌላ መዘዝም ያስተዋውቀናል፡፡ ያም የተቺዎቹ ቁጥር እያደገ መምጣቱና በብርቱ ሊቃወሙት መጀመራቸው ነው፡፡ እንዲያውም፣ ክፍሉ የሚጠናቀቀው የኢየሱስን ሞት

በማመልከት ነው፡፡ በማርቆስ 3፥6 ውስጥ፣ የኢየሱስ ተቃዋሚዎች በጣም መቆጣታቸውን እና አብዛኞቹም እርሱን ለመግደል ማሴር መጀመራቸውን ማርቆስ ይዘግብልናል፡፡

***ኢየሱስ ተቀባይነትን ያጣው በትምህርቶቹና በተዓምራቶቹ ምክንያት ነው፡፡ አዲስ ኪዳንን ስናነብብ፣ ሰዎች ለምን አልተቀበሉትም? ለምንስ ኃይሉን ማየት ተሳናቸው? ለምንስ ትምህርቶቹን ማድመጥ አቃታቸው? ብለን እናስባለን፡፡ ግን የኢየሱስ ትምህርቶች … ሰዎች የሚቃወሟቸውን በርካታ ነገሮች ይዘዋል፡፡ አንደኛው ይዘቱ ሰዎች የሚፈልጉት ዓይነት አልነበረም፡፡ እነርሱ የሚጠብቁት ምድራዊ መንግሥት ነው፡፡ እርሱ የሚናገረው ግን በሰዎች ልብ ስለምትመጣውና የሰዎችን ሕይወት ስለምታድሰው፣ በሰዎች ልብ ውስጥ እግዚአብሔር ስለሚነግሥባትና ስለሚዛባት መንግሥት ነው፡፡ በተጨማሪም ትምህርቱ ልብን ሰንጥቆ የሚገባ መሆኑም ነው፡፡ በእርግጥም ተዓምራቱ ይበልጡኑ የሚጠሉ ነበሩ፣ ምክንያቱም በትምህርቶቹ የማይስማሙት የክርስቶስ ጠላቶች ተዓምራቱ በአንድ መንገድ የሚናገረውን ነገር የሚያረጋግጡ ሊሆኑ እንደሚችሉ ስለሚያውቁ ነው፡፡ የእግዚአብሔርን አስተምህሮ የወደቀው ልብ በተፈጥሮአዊ መንገድ ወይም በዝግጁነት ሊቀበለው አይችልም፣ የእግዚአብሔር አስተምህሮ ደግሞ የዚህ ነገር አንጸባራቂ ምሳሌ ነው፣ ያም ማለት እግዚአብሔር በሰዎች መካከል ሰዎች ግን አልተቀበሉትም ማለት ነው፡፡ (ዶ/ር ጄፍ ሎውማን)***

***እኛ አብዛኛውን ጊዜ ወደ እግዚአብሔር የምንመጣው የራሳችንን አጀንዳዎች ይዘን ነው፡፡ ምን ሊመስል እንደሚገባውና እንዴት ሥራውን ማከናወን እንዳለበት የራሳችን ግምት ይኖረናል፡፡ የእኛን አጀንዳዎች፣ ግምቶቻችንን ከተቃወመ፣ አብዛኛውን ጊዜ መታገሥ አንችልም፡፡ እናም፣ ኢየሱስ እነርሱ ከሚጠብቁት መንግሥት ጋር የማይጣጣም መንግሥት እየሰበከ ሲመጣ ሰዎች ጠሉት፡፡ እርሱ መሲህ ሆኖ ቢመጣም፣ እነርሱ አስቀድሞ መሲሑ ይመስላል ካሉት ጋር የሚጣጣም አልሆነም፡፡ እናም የእነርሱን ግምት ሊያረጋጋው አልቻለም፡፡ እናም ያን መሳዩን ነገር አንወድደውም፡፡ አንዳንድ ጊዜ ኢየሱስ የሚጠላው የሃይማኖቱ መሪዎች ከነበራቸው ዕቅድ የተለየ እቅድ ይዞ ስለመጣ ነበር፡፡ እነርሱ በነበራቸው የሃይማኖት ሃላፊነት ሊኖራቸው የሚፈልጉትን ክብር፣ ገዢነት፣ ሥልጣን  እና ኃይል የሚደመስስ መንግሥት እየሰበከ መጣ እነርሱ ደግሞ ከዚያ ጋር ምንም ንክኪ እንዲኖራቸው አልፈለጉም፡፡ እናም በየትኛውም ወቅት የራሳችንን አጀንዳዎች ይዘን ወደ እግዚአብሔር ከመጣን፣ በትሁት ልብ ፣ በሚማር ልብ ወደ እርሱ ከመቅረብና በመንገዳችን ላይ በሚያመጣቸው ነገሮች ሁሉ ላይ በእርሱ ከመታመን ይልቅ፣ ራሳችንን የእግዚአብሔር ተቃዋሚ እናደርጋለን፡፡ (ዶ/ር ኬ. ኤሪክ ቶኔስ)***

በቅፍርናሆም አቅራቢያ ኢየሱስ ያከናወናቸውን ተግባራት ከዳሰስን፣ በማርቆስ 3፥7 - 6፥13 እንደተፃፈው አገልግሎቱ በመላው የገሊላ አውራጃ እንዴት እንደተስፋፋ እንመልከት፡፡

## የገሊላ አውራጃ

በዚህ ወቅት፣  ኢየሱስ በአዳዲስ አካባቢዎች፣ ማለትም ከቅፍርናሆም ባሻገር ወደ ተቀሩት አካባቢዎች የእግዚአብሔር መንግሥት የቀረበች መሆኑን ሰብኳል አሳይቷልም፡፡ በነዚህም አካባቢዎች ንስሓንና እምነትን ሲሰብክ፣ ህዝብ ይሰበሰብ ነበር እናም የጠነከረ ተቃውሞም ይቀሰቅስ ነበር፡፡

ይህ ክፍል የሚጀምረው በማርቆስ 3፥7-12 ኢየሱስ ከመንጋው ገለል ማለቱን በማመልከት ነው፡፡

ይህ አንቀጽ የተቀረውን ክፍል ሁኔታ የሚገልጥ ሲሆን ምንም እንኳን እርሱ ሊቀንሰው ቢሞክርም፣ የኢየሱስ ዝና በየአካባቢው መውጣቱን በአፅንዖት ያሳየናል፡፡ በውጤቱም በዙሪያው  የተሰበሰበው መንጋ

እንዳያገለግል እንቅፋት ሲሆንበት እናያለን፡፡ ኢየሱስ በገሊላ የተቀሩ አካባቢዎች አገልግሎቱን እንዲያሰፋ ያደረገው አንዱ ምክንያት ይህ ችግር ነው፡፡

በማርቆስ 3፥13-19 እንደምንመለከተው፣ የዚህ ትረካ ቀጣይ ክፍል ኢየሱስ ከእርሱ ተከታዮች መካከል የእርሱ ልዩ ደቀመዛሙርት እንዲሆኑ ዐሥራ ሁለቱን መምረጡን ይዘግባል፡፡

ኢየሱስ ዐሥራ ሁለቱን ደቀመዛሙርት የመረጠው ወንጌልን በመስበክና ተዓምራትን በማድረግ አጋሮቹ እንዲሆኑ ነው፡፡ ማርቆስ ግን ከእነርሱ መካከል አንዱ ኢየሱስን አሳልፎ እንደሚሰጥ አንባቢዎቹን ያሳስባቸዋል፡፡ ኢየሱስን የመቃወሙ ነገር ከጠላቶቹ ብቻ ሳይሆን፣ ከቅርብ ተከታዮቹም እንኳን እንደሚነሳ ያሳያል፡፡

ከዚህ በኋላ፣ በማርቆስ 3፥20-35 እንደምንመለከተው ኢየሱስ ከህጉ መምህራን እና ከገዛ ቤተሰቦቹ ስለ ደረሰበት ተቃውሞ ማርቆስ ይዘግብልናል፡፡

ይህ ትረካ የሚያሳየን ኢየሱስ በተዓምራዊ ኃይል የመንግሥቱን ወንጌል በሰበከ ቁጥር፣ ከሁሉም አቅጣጫ ተቃውሞ የሚነሳበት መሆኑን ነው፡፡ የህጉ መምህራን እርሱን እንደ መሲህ ከመቀበል ይልቅ፣ ኢጋንንት እንዳደረበት ያምኑ፣ ቤተሰቦቹም አዕምሮውን ስቷል ብለው ያምኑ ነበር፡፡

ይህንን ተከትሎ፣ በማርቆስ 4፥1-34 ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ምሳሌዎችን በማቅረብ ኢየሱስ ወንጌልን ይሰብክ ነበር፡፡

አብዛኛውን ጊዜ ኢየሱስ በማያምኑ ሲከበብ በምሳሌ ያስተምር ነበር፡፡ ይህንንም የሚያደርገው የሚያምኑት የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመግለጥ፣ ከማያምኑት ደግሞ ለመሰወር ነበር፡፡ በማርቆስ 4፥11-12 ይህንን ለደቀመዛሙርቱ ነግሯል፡

> ***ለእናንተ የእግዚአብሔርን መንግሥት ምሥጢር ማወቅ ተሰጥቶአችኋል፤ በውጭ ላሉት ግን፥ አይተው እንዲያዩ እንዳይመለከቱም፥ ሰምተውም እንዲሰሙ እንዳያስተውሉም፥ እንዳይመለሱ ኃጢአታቸውም እንዳይሰረይላቸው ነገር ሁሉ በምሳሌ ይሆንባቸዋል። (ማር 4፥11-12)***

የሚያሳዝነው ግን፣ አንዳንድ ጊዜ የኢየሱስ ምሳሌዎች የራሱንም ደቀ መዛሙርት ግራ ያጋባ ነበር፡፡ ይህ ሲከሰት ግን፣ በትክክል የተረዱት መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኢየሱስ ፍቺውን ይነግራቸው ነበር፡፡

በማርቆስ ትረካ በዚህኛው ክፍል ውስጥ ያለው ዋና ነጥብ እግዚአብሔር የመንግሥቱን ሙላት የሚያመጣው በወንጌል መስፋፋት በኩል በሚገለጥ ረጅም ሂደትና የቀስ በቀስ እድገት መሆኑን ማሳየት ነው፡፡ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወደ ምድር አምጥቷል፡፡ ያደረገው ግን ልክ እርሱ እንዳለፈበት ሁሉ የእርሱም ተከታዮች መከራን በመጋፈጥ ውስጥ በሚያልፉበት እጅግ በረዘመ መንገድ እነዲሆን ነው፡፡

ስለ ኢየሱስ ምሳሌዎች ማርቆስ ያቀረበው ዘገባ በማርቆስ 4፥35-5፥43 እንደተገለጠው በርካታ የኃይሉን መገለጫዎች ያስከተለ ነው፡፡

በዚህ ስፍራ፣ ማርቆስ ኢየሱስ አየሩን የሚቆጣጠር፣ ኢጋንንት የሚያስወጣ፣ በሽታን የሚፈውስ እና ሙታንን የሚያስነሳ መሆኑን ዘግቧል፡፡ በእያንዳንዳቸው በነዚህ ታሪኮች ውስጥ፣ ሰዎች በገጠሟቸው አደጋዎች

ተደናግጠው ነበር። ኢየሱስ በተዓምራቱ ካዳናቸው በኋላ ግን፣ ድንጋጤአቸው ጨምሮ ነበር። ምክንያቱም ይህንን ሁሉ ኃይል የተሸከመው ሰው በእውነት ማን እንደሆነ አላወቁም ነበር።

*የኢየሱስ ተከታዮች የነበሩት፣ ደቀመዛሙርት፣ በወንጌላት ውስጥ አንዳንድ ጊዜ ፍርሃት ይታይባቸው የነበረው ኢየሱስ አስደናቂ ተዓምራትን ሲያደርግ በሚከሰቱት ድራማዊ ነገሮች ነበር። እግዚአብሔር ሥራውን ሲሠራ ይፈራሉ። ለምሳሌ በማርቆስ 4 ውስጥ፣ ደቀ መዛሙርቱ በባህሩ ላይ በታላቅ ማዕበል ውስጥ ነበሩ። ማዕበሉ ትንኳቸውን ያናውጠው እና ጀልባዋም ልትሰጥም ትቃረብ ነበር፣ ኢየሱስ ግን ትራስ አድርጎ ተኝቶ ነበር። እነርሱም ከጀልባዋ ውሃን በማፍሰስ ይረዳናል በሚል ተስፋ ኢየሱስን "ጌታ ሆይ፣ ስንጠፋ አይገድህምን?" በማለት ቀሰቀሱት። ኢየሱስም ተነሣና ማዕበሉም ነፋሱም ፀጥ እንዲሉ ነገራቸው። ከማዕበሉ የተነሳ ፈርተው ነበር፣ አሁን ግን ዳኑ፣ ማርቆስ ግን ታላቅ ፍርሃት ወደቀባቸው ብሎ ይነግረናል። ታዲያ ምን አስፈራቸው? ማእበሉ የለም፤ ውሃውም ፀጥ ብሏል። የፈሩበት ምክንያት ነፋስንና ማዕበልን ፀጥ ማሰኘት የሚችለው ነፋስንና ማዕበልን የፈጠረ እግዚአብሔር ራሱ ብቻ እንደሆነ ስለሚያውቁ ነው። አሁን በመርከብ ውስጥ አብረው ያሉት ማዕበሉንና መጀቡን ፀጥ ካደረገው ከእግዚአብሔር ጋር መሆኑን ተረድተዋል። ያም በእነርሱ ውስጥ ፍርሃትን የፈጠረው ይህ ምን ዓይነት አምላክ እንደሆነ ገና አለማወቃቸው ይመስለኛል። ግራ ወደ መጋባት ውስጥ የገቡ እና የኢየሱስን ባህርይ ያላወቁ ይመስላሉ። (ዶ/ር ፍራንክ ቴይልማን)*

ይህንን የኃይል አገልግሎት በማስከተል፣ ማርቆስ የጻፈው በማርቆስ 6፥1-6 ኢየሱስ በገዛ ከተማው በናዝሬት የገጠመውን ተቃውሞ ነው። ትረካው ኢየሱስ በዚህ የአገልግሎቱ እርከን ላይ ከበርካታ ሰዎች ብርቱ ተቃውሞ የገጠመው መሆኑን እንደገና አፅንዖት በመስጠት ያወሳል። ወንጌሉ ከኃይል ጋር ቢስፋፋም፣ የሚከተለው ህዝብ ቢበዛም፣ የገዛ ከተማው ሰዎች እርሱንና ወንጌሉን ተቃውመዋል።

በመጨረሻ፣ በገሊላ የነበረው የኢየሱስ አገልግሎት ዘገባ የሚያበቃው በማርቆስ 6፥7-13 በተመዘገበው ዐሥራ ሁለቱን ደቀመዛሙርቱን በመላኩ ላይ ነው። በፓለስታይን ምድር ዙሪያ የመንግሥቱን ወንጌል እንዲሰብኩና ተዓምራትን እንዲያደርጉ 12 ደቀመዛሙርቱን ኢየሱስ ላካቸው። ሆኖም ደቀመዛሙርቱ የንስሓንና የእምነትን ወንጌል በሚሰብኩበት ወቅት ሰዎች ምላሽ የሚሰጧቸው ለእርሱ ምላሽ በሰጡበት መንገድ እንደሚሆን ኢየሱስ ግልፅ አድርጎላቸዋል። አንዳንዶች ይቀበሏቸዋል፣ ሌሎች ደግሞ አይቀበሏቸውም። ተቃውሞው ቢበዛም የእግዚአብሔር መንግሥት ግን ማደጓን እንደምትቀጥል ኢየሱስ በጽናት አስተምሯል።

በቅፍርናሆም ከተማና በአካባቢዋ የገሊላ አውራጃዎች የኢየሱስን የወንጌል አገልግሎት ከዘገበ በኋላ፣ በማርቆስ 6፥14-8፥26 ውስጥ ከገሊላ ባሻገር በኢየሱስ አገልግሎት የተገለጠውን የመሲሁን ኃይል ወደ መዘገቡ ማርቆስ ዘወር ይላል።

## ከገሊላ ባሻገር

ከገሊላ አውራጃ ባሻገር የኢሱስን ሥራዎች ሲዘግብ፣ አስቀድመን በተመለከትናቸው ዋና ርዕሰ ጉዳዮች ላይ አፅንዖት መስጠቱን ማርቆስ ቀጥሎበታል። የመንግሥቱ አዋጅ በኃይል መታወጅ መቀጠሉን፣ በአድናቆት የተሞሉ ሰዎችን ምላሽ እና የኢሱስ ተቃዋሚዎች ቁጥር መጨመሩን ዘግቧል።

ሆኖም ማርቆስ በደቀመዛሙርቱ ላይ በአዲስ መንገድ ትኩረት ያደርጋል። ወደፊት ለሚመጡት አስቸጋሪ ቀናት ኢየሱስ እነርሱን ባሰለጠነበት መንገደ ላይ አፅንዖት ሰጥቷል። በተደጋጋሚ እርሱ የሚያስተምራቸውን

ትምህርቶች በትክክል ስለማይረዱበት መንገድና ለእርሱ ባላቸው መሰጠት በሚደክሙባቸው ነገሮች ላይ ትኩረታቸውን ይስብ ነበር።

ኢየሱስ ከገሊላ ባሻገር የሰጠው አገልግሎት የማርቆስ ዘገባ የሚጀምረው በማርቆስ 6፥14-29 በተመዘገበው በኢየሱስ ዝና መውጣት ላይ አፅንዖት በመስጠት ነው።

ባለፈው ጊዜ፣ ኢየሱስ አገልግሎቱን በቅፍርናሆም ዙሪያ ሲገድበው፣ ዝናው ግን በገሊላ አውራጃዎች ሁሉ ተስፋፋ። አሁን ደግሞ ዝናው ከእርሱ መቅደሙን ቀጥሏል። ኢየሱስ ገና በገሊላ ጫፍ ላይ እያለ፣ ዝናው ግን በመላው ፓለስታይን እንዲያውም ወደ ንጉሡ ሄሮድስም ወጥቶ ነበር። ማርቆስ ይህንን አጋጣሚ ስለ ኢየሱስ ማንነት ለተነሳው ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት ተጠቅሞበታል። በተለይም፣ ንጉሥ ሄሮድስ መጥምቁ ዮሐንስን እስካስገደለው ድረስ፣ ኢየሱስ መጥምቁ ዮሐንስ ሊሆን እንደማይችል ማርቆስ አብራርቷል።

ቀጥሎም፣ ማርቆስ በማርቆስ 6፥30-56 ውስጥ የተለያዩ ተዓምራትን ዘግቧል። ይህ የመጀመሪያው ክፍል ኢየሱስ ዘወር ለማለት መሞከሩን፣ ግን ወዲያው ቀጥሎ መንጋው አስቀድሞው ለምን እንደተሰበሰበ የሚሳዩ በርካታ የኃይል ሥራዎችን ይገልጣል። ኢየሱስ ኃይሉን የገለጠው 5000 እና 4000 ሰዎችን በመመገብ፣ በገሊላ ባህር ላይ በመራመድ እና ደንቆሮና ዲዳውን በመፈወስ ነበር። ተዓምራቶቹ ማንም ሊከዳቸው የማይችለውን በተፈጥሮ ላይ ያለውን ኃይል የሚያሳዩ ነበሩ። በእነዚህም ኃይለኛ ተዓምራት ምክንያት፣ ህዝቡ ኢየሱስን በሄደበት ሁሉ ይከተሉት ነበር። አንዳንድ ጊዜም ከእርሱ ይቀድሙ ነበር።

የኢየሱስን ተዓምራት በማስከተል፣ በማርቆስ 7፥1-23 ውስጥ ቀጣዩን የፈሪሳውያን ተቃውሞ ማርቆስ ይዘግብልናል። ኢየሱስና ፈሪሳውያኑ የብሉይ ኪዳንን ህግ በተገቢው መንገድ ስለመጠበቅ፣ የትውፊትን እሴት አስመልክቶ እና የቅድስናን ምንነት በተመለከተ ይከራከሩ ነበር። በውጤቱም፣ በኢየሱስና በአይሁድ ፓርቲ ውስጥ ተፅዕኖ ፈጣሪ በነበሩት መካከል ያለው ውጥረት ከረረ።

በመጨረሻ፣ በማርቆስ 7፥24-8፥26 ሌሎች ተዓምራቶችን ማርቆስ ይዘግብልናል። ይህ ክፍል የሚጀምረውና የሚያበቃው ኢየሱስ መንጋውን ዘወር ለማድረግ ወይም ሊከላከል መሞከሩን በሚገልጠው ዐረፍተ-ነገር ነው። በዐረፍተ-ነገሮቹም መካከል፣ ኢየሱስ በአይሁድና በአህዛብ መካከል በርካታ ተዓምራትን ማድረጉን ይዘግባል። አንዳንድ አህዛብም በእርሱ ማመናቸውንም ይዘግባል።

በእነዚህ ተዓምራቶች መሃል፣ ለኢየሱስ ደቀመዛሙርት ድክመት ማርቆስ ልዩ ትኩረት ይሰጣል። በአገልግሎቱ ጅማሬ ላይ፣ በማርቆስ 4፥13 እንደምንመለከተው፣ ደቀመዛሙርቱ የዘሪውን ምሳሌ አልተረዱም ነበር። በዚም ወቅት፣ አንዳንዶቹን ትምህርቶቹን ገና መረዳት አልቻሉም ነበር። ስለዚህ፣ ኢየሱስ በቀጥታ ተቃወማቸው። በማርቆስ 8፥14-17 ማርቆስ የዘገበውን አድምጡ፡

> **እንጀራ መያዝም ረሱ፥ ለእነርሱም ከአንድ እንጀራ በቀር በታንኳይቱ አልነበራቸውም። እርሱም፦ ተጠንቀቁ፤ ከፈሪሳውያንና ከሄሮድስ እርሾ ተጠበቁ ብሎ አዘዛቸው። እርስ በርሳቸውም። እንጀራ ስለሌለን ይሆናል ብለው ተነጋገሩ። ኢየሱስም አውቆ እንዲህ አላቸው፦ እንጀራ ስለሌላችሁ ስለ ምን ትነጋገራላችሁ? ገና አልተመለከታችሁምን? አላስተዋላችሁምን? (ማርቆስ 8፥14-17)**

ኢየሱስ ይናገር የነበረው ስለ መንፈሳዊው መበላሸት ነበር፣ ደቀመዛሙርቱ ግን ወደ ሆዳቸው ስለሚገባው እንጀራ የሚያወራ መሰላቸው። ኢየሱስ ለምን በእነርሱ ተስፋ እንደቆረጠ በቀላሉ መመልከት ይቻላል።

ኢየሱስ እንደ መሲህ የገለጠውን ኃይል አስመልክቶ ማርቆስ ባቀረባቸው ዘገባዎች ሁሉ ውስጥ፣ የኢየሱስ ተዓምራትና ትምህርቶች እርሱ በእውነት ክርስቶስ መሆኑን የሚያረጋግጡ ነበሩ፡፡ ታዲያ፣ ለምን ብዙ ህዝብ ይቃወመዋል? ለምን አልተቀበሉትም? የእርሱ ደቀ መዛሙርት እንኳን ሳይቀሩ እርሱን የመረዳትና የመከተል ችግር ለምን ገጠማቸው? በትልቁ ምክንያቱ ኢየሱስ ሰዎች ይጠብቁት የነበረው ዓይነት መሲህ አለመሆኑ ነበር፡፡ እነርሱ እንደሚጠብቁት የፖለቲካ የበላይነትን ከማምጣት ይልቅ፣ ኃይሉን ይጠቀም የነበረው ወንጌልን ለመስበክና የሌሎችን መሻት ለማሟላት ነበር፡፡

*ከመጀመሪያው ምዕተ-ዓመት የምናገኘው መረጃ እንደሚያሳየን አይሁድ ይጠብቁት የነበረው፣ ፖለቲካዊና ወታደራዊ መሲህ፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚያመጣ፣ ሮማውያንን የሚያስወጣ፣ ሮማውያንን ድል የሚነሳ እና ኢየሩሳሌምን ማዕከል አድርጎ የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚመሠርተውን ነበር፡፡ በዚያም ረገድ በጣም ብሔርተኝነት የሚንፀባረቅበት ነበር፡፡ ኢየሱስ ደግሞ ያንን የብሐየርተኝነት ስሜት የሚያረካ ምንም ምልክት አላሳየም፤ ይልቁኑ እጅግ ታላቅ ራዕይ ነበረው፡፡ ጉዳዩ ስለ ሮማውያን አልነበረም፤ ስለ ፍጥረት ስለ ራሱ ነበር እንጂ፡፡ ፍጥረት በውድቀት ውስጥ ነበር፣ እናም ኢየሱስ የመጣው ይህን የውድቀት ገፅታ ለመቀልበስ፣ አንድ ጊዜም እንደገና የእግዚአብሔርን መንግሥት በምድር ለመመሥረት ነበር፡፡ ያም መንግሥት ኃጢአትን ድል የሚነሳ፣ ሰይጣንን ድል የሚነሳ እና ሞትን ድል የሚነሳ ነው፡፡ ስለዚህ ኢሱስ ይመለከት የነበረው ከተራ ፖለቲካዊ እና ወታደራዊ ድል የበለጠ ነገርን ነበር፡፡ (ዶ/ር ማርክ ስትራውስ)*

*የአይሁድ ህዝብ ለአምስትና ለስድስት መቶ ዓመታት ሲጠብቅ የነበረው የዕስራኤልን መንግሥት ወደ ነበረበት የሚመልስላቸውን አንድ ሰው ነበር፡፡  ንጉሥ አልነበራቸውም፤ ነፃነትም አልነበራቸውም፡፡ ስለዚህ በመጀመሪያው ምዕተ-ዓመት የፓለስታይን ምድር ውስጥ ትልቅ ውጥረት ነበር፣ ምክንያቱም ኢየሱስ መንግሥቱን ሲያውጅ እና መሲህ የመሆኑን ፍንጭ ሲያሳይ፣ የሚናገረውን ለመስማት አቆብቁበው ነበር፡፡ ለመሆኑ ምን ይጠብቁ ነበር? አዎን፣ ይጠብቁ የነበረው መቅደሱን እነደገና የሚሠራላቸውን፤ እንዲያውም በዚያ ዘመን በእርግጥ ይህ በአረማዊ ንጉሥ የተሠራ መቅደስ እግዚአብሔር እንዲሆን የሚፈልገው ነውን? የሚል ጥርጣሬም ነበር፡፡ ከዚያም የበለጠ ግን፣ እግዚአብሔር እስራኤልን እንዲቤዥ፣ በብሉይ ኪዳን የገባቸውንም ተስፋዎች እንዲፈፅም ይናፍቁ ነበር፡፡ ታዲያ እግዚአብሔር ተስፋውን የሚፈፅመው የት ነው? እናም እነርሱ በተለይ የሚጠብቁት ያንን ነበር፣ ግን ያንን ጥርጣሪ ሲያስተጋቡ ማለት የፈለጉት፣ እኛ እንደሆነ በሮማውያን ወረራ ስር ነን፣ እግዚአብሔር በእርግጥ ተስፋዎቹን የሚፈፅም ከሆነ፣ ሮማውያንን ማስወጣት ይገባዋል የሚል ነበር፡፡ ምናልባትም የሚጠብቁት ፖለቲካዊ ነፃነትን ሊሆን ይችላል፡፡ በአዲስ ኪዳን ደግሞ፣ ኢየሱስ መሲህ ነኝ ብሏል፣ ያም ማለት መቅደሱን መልሶ የሚሠራ፣ እንዲያውም እርሱ እውነተኛው መቅደስ ነው፣ በተጨማሪም እርሱ መንግሥቱንም የሚያመጣ ነው፣ ግን በእርግጥም ፖለቲካዊ ነፃነት ያለው የአይሁድ መንግሥት ግን አልተመሠረተም፡፡  እንደ እውነቱ፣ ዜናው  ኢየሱስ ክርስቶስ ንጉሡ የዓለም ሁሉ ጌታ ነው የሚለው ሆኖ ነበር፡፡ ስለዚህም፣ እነርሱ ይጠብቁት ከነበረው መጠነኛ ልዩነት ነበረው፡፡ (ዶ/ር ፒተር ዎከር)*

የማርቆስ ቀደምት ተደራሲያን ምናልባትም ዐሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ገጥሟቸው በነበረው ኢየሱስ እንዴት ዓይነት መሲህ ነው የሚለው ተመሳሳይ ውጥረት ገጥሟቸው ይሆናል፡፡ በሮም የምትገኘው ቤተክርስቲያን የተመሠረተችው ክርስትና ጥሩ ተቀባይነት በነበረው ዘመን ነበር፡፡ እንደ አብዛኞቹ ቀደምት አብያተ ክርስቲያናት፣ እነርሱም ኢየሱስ በቶሎ እንደሚመጣና መንግሥቱንም በምድር እንደሚመሠርት ይጠብቁ ነበር፡፡ በምትኩ ግን፣ ዓመታቶቹ በኔሮ ዘመን የሆነውን አሰቃቂ መከራና ስደት አመጡባቸው፡፡ ስለዚህም፣ ማርቆስ ኢየሱስ ምንም እንኳን ዘወትር ተከታዮቹ የሚጠብቁትን ነገር ባያደርግም መቼም ቢሆን ኃያሉ መሲህ ሆኖ የሚዘልቅ መሆኑን ግልፅ አድርጓል፡፡ እርሱ ኃያል መሲህ በመሆኑ ምክንያት፣ ልክ ተስፋ

በሰጠበት መንገድ በትክክለኛው ሰዓት፣ መንግሥቱን በድል ያመጣል በማለት ክርስቲያኖች ያምናሉ፡፡ ሆኖም እስከዚያው ድረስ፣ እርሱ አሁንም ጌታ ነው፣ እናም በምንም ዓይነት መከራ ውስጥ ብናልፍም እርሱ ያፀናናል፡፡

የመሲሁን ኃይል ከሚገልጠው ረጅም የማርቆስ ትረካ በኋላ፣ ወደ ወንጌሉ ሦስተኛ ዐቢይ ክፍል እንሸጋገራለን፡፡ ያም በማርቆስ 8፥27-30 ባለው ክፍል ሐዋርያት ስለ መሲሁ የሰጡትን ማረጋገጫ የያዘ አጭር ምእራፍ ነው፡፡

## ስለ መሲሁ ሐዋያት የሰጡት ማረጋገጫ

ይህ ወደ ፊሊጶስ ቂሳርያ በተደረገ ጉዞ ላይ የታየ አስደናቂ ትዕይንት ሲሆን ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ መሆኑን ደቀ መዛሙርቱ እንዲያወጡ ያደረገበት ነው፡፡ እናም ሁሉም በማርቆስ ወንጌል ላይ ጥናት ያደረጉ ምሁራን እንደሚስማሙት ነገሩ የማርቆስ ወንጌል ማዕከላዊ ሃሳብ ነው፡፡

በወንጌሉ የመጀመሪያ ጥቅስ፣ ማርቆስ "**የእግዚአብሔር ልጅ፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል *መጀመሪያ***" ሲል ጽፏል፡፡ ኢየሱስ "**ክርስቶስ፣**" ***መሲህ ነው***፡፡ ሆኖም በዚያ ጥቅስ፣ "**ክርስቶስ**" በማርቆስ ወንጌል በየትኛውም ስፍራ ተገልጦ አናየውም፡፡ ማርቆስ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ብሎ አልተናገረም፡፡ ደቀ መዛሙርቱ ክርስቶሰ ብለው ጠሩት ብሎም አልዘገበም ወይም ስለ እርሱ የመሰከሩ ሰዎች እርሱ ክርስቶስ ነው ብለው አልገመቱም ወይም ኢጋንንትም ክርስቶስ የሚለውን ስም ተጠቀሙ አይልም፡፡

እንዲያውም፣ ኢየሱስን እንዲህ ነው ሊል የሞከረ ሁሉ ተሳስቶ ነበር፡፡ ተራ ጠዓምራት አድራጊ ወይም ነቢይ ወይም መጥምቁ ዮሐንስ ወይም ንክ ወይም ብኤል ዜቡል ያደሩበት ነው ብለው ያስቡ ነበር፡፡ በዚህ ወቅት ግን፣ ደቀ መዛሙርቱ በእውነት እርሱ ማን ስለመሆኑ እውቅና እንዲሰጡ ይገፋቸዋል፡፡ እስኪ በማርቆስ 8፥27-29 ያደረጉትን ንግግር አድምጡ፡፡

> ***ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱም በፊልጶስ ቂሣርያ ወዳሉ መንደሮች ወጡ በመንገድም። ሰዎች እኔ ማን እንደ ሆንሁ ይላሉ? ብሎ ደቀ መዛሙርቱን ጠየቃቸው።***
> ***እርሱም፦ መጥምቁ ዮሐንስ፥ ሌሎችም ኤልያስ፥ ሌሎችም ከነቢያት አንዱ ብለው ነገሩት። እናንተስ እኔ ማን እንደ ሆንሁ ትላላችሁ? ብሎ ጠየቃቸው። ጴጥሮስም፦ አንተ ክርስቶስ ነህ ብሎ መለሰለት። (ማርቆስ 8፥27-29)***

ከ8 ምዕራፎች ማስረጃ በኋላ፣ ሐዋርያት በስተመጨረሻው ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚያመጣው መሲሁ፣ እንደሆነ እንደሚያምኑ አረጋገጡ፡፡

ስለ መሲሁ ሐዋርያት ከሰጡት ማረጋገጫ በኋላ፣ አራተኛው የማርቆሰ ወንጌል ዐቢይ ክፍል የሚያወሳው ስለ መሲሁ መከራ ነው፡፡ ይህ ክፍል ከ 8፥31-15፥47 ይዘልቃል፡፡

በመጀመሪያው የወንጌሉ ኢጋማሽ፣ የኢየሱስ የኃይል አገልግሎት እንዴት ክርስቶስነቱን ወዳረጋገጠው የከበረ እርከን እንዳመራ ማርቆስ ትኩረት አድርጓል፡፡ በዚህ ነጥብ ግን፣ ማርቆስ በኢየሱስ መሲሃዊ ሥራዎች ልዩ ልዩ ገፅታዎች ላይ አፅንዖት መስጠት ይጀምራል፡፡ ይህም በኢየሩሳሌም የገጠመው መከራና ሞት ነው፡፡

# መከራን የተቀበለው መሲህ

የማርቆስ ወንጌል ስለ መሲሁ መከራ የሚናገረው ክፍል በሦስት ዋና ክፍሎች ይከፈላል፡ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ለመከራውና ለሞቱ ማዘጋጀቱን፣ መከራውንና ሞቱን ያፋጠነውን ግጭት ከአይሁድ መሪዎች ጋር ማድረጉን እና በስተመጨረሻም መከራና ሞትን መቅመሱ ናቸው፡፡ በማርቆስ 8፥31 - 10፥52 በተገለጠወ በዝግጅቱ በመጀመር ሁሉንም በየተራ እንቃኛለን፡፡

## ዝግጅት

ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ስላዘጋጀበት የሚወሳው ክፍል በሦስት ዋና ክፍሎች ይከፈላል፣ ሁሉም ስለ መከራው፣ ስለ ሞቱና ስለ ትንሣኤው አስቀድሞ በመናገሩ ይጀምራሉ፡፡ በማርቆስ 8፥31-9፥29 የሚገኘው የመጀመሪያ ክፍል ኢየሱስ የመንግሥቱ ጌታ በመሆኑ ላይ ያተኩራል፡፡

ማርቆስ የሚጀምረው የእግዚአብሔርን የከበረ መንግሥት መንግሥት ወደ ምድር ለማምጣት ኢሱስ የተከተለውን የማይጠበቅ ስልት ማለትም የኢየሱስ መከራ፣ ሞትና ትንሣኤ በመዘገብ ሲሆን ያንንም ማርቆስ በ8፥31-9፥1 አብራርቶታል፡፡ በዚህ ክፍል ባቀረባቸው ትምህርቶች፣ ኢየሱስ ስለ መከራው ያወሳ ሲሆን፣ ደቀ መዛሙርቱም የእርሱን የወንጌል አገልግሎት ሲቀጥሉም መከራን ሊቀበሉ እነዳላቸው ያስጠነቅቃቸው ነበር፡፡

ከዚህ በኋላ፣ ማርቆሰ በተለምዶ መለወጥ ብለን ወደ ምንጠራው እና ለየት ያለ ሥልጣኑን ወዳሳየበት ክስተት ማርቆስ 9፥2-13ትኩረታችንን ይስበዋል፡፡ በዚህ ሁነት፣ የኢየሱስ ክብር ለጴጥሮስ፣ ለያዕቆብ እና ለዮሐንስ በገሃድ ተገልጧል፡፡ ሙሴና ኤልያስም ከኢየሱስ ጋር ታይተዋል፣ ያም ኢየሱስ የሙሴን ህግና የነቢያቱን ቃል ያፀና እና ማስተማሩንም የቀጠለ መሆኑን ያመለክታል፡፡ እግዚአብሔር ግን ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስን ከሙሴና ከኤልያስም ይልቅ ሊያከብሩና ሊታዘዙት እንደሚገባ አዝዟቸዋል፡፡ ይህ ሁኔታ ደቀ መዛሙርቱ ከሌሎቸ ሁሉ ይልቅ ለኢየሱስ ታማኝ ሆነው እንዲዘልቁ ያም ታማኝነት ለእግዚአብሔርና ለብሉይ ኪዳኑ መገለጥ ከነበራቸው ታማኝነት የወጣ ሊሆን እንደሚገባው የሚያሳስብ እና የሚዘጋጅ ነበር፡፡

በመጨረሻም፣ ማርቆስ አጋንንቶችን በማዘዝ ላይ ኢየሱስ ያለውን ሥልጣን በማርቆስ 9፥14-29 ውስጥ በመግለጥ በኢየሱስ ልዩ ኃይል ላይ አተኩሯል፡፡ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት አንድን አስቸጋሪ አጋንንት ማስወጣት አልቻሉም እናም ኢየሱስ ያንን መሳይ አጋንንት በጸሎት ብቻ ሊወጣ እንደሚችል አስተማራቸው፡፡ ኢየሱስ ራሱ ግን በቀላል ትእዛዝ አጋንንትን ማስወጣት ይችላል፡፡ በዚህ መንገድ፣ ከሌሎቹ ሁሉ የሚበልጥ መሆኑን ያሳየ ሲሆን፣ ፈቃዱንም ለመፈፀም ያልተገደበ ኃይል ያለው መሆኑን ለደቀመዛሙርቱ አረጋግጦላቸዋል፡፡ እርሱ በተገደለበት ወቅት የገጠማቸው ጥርጥርና ፍራቻ እንዳለ ሆኖ፣ የእርሱ ባላቸው እምነት እንዲፀኑ የእርሱ ኃይል አበረታትቷቸዋል፡፡

ኢየሱስ ለመከራ፣ለሞትና ለትንሣኤ ያደረገውን ዝግጅት የሚያሳየው ሁለተኛው የማርቆስ ወንጌል ክፍል ስለ እግዚአብሔር መንግሥት እሴቶች የሚወራ ሲሆን፣ በማርቆስ 9፥30-10፥31 ውስጥ ይገኛል፡፡

ኢየሱስ ለኢየሩሳሌም ስለመዘጋጀቱ እንደሚያወሱት ልክ እንደሌሎቹ የማርቆስ ወንጌል ክፍሎች ሁሉ፣ ይህኛውም ኢየሱስ መከራውን፣ ሞቱንና ትንሣኤውን አስቀድሞ በመናገሩ ይጀምራል፡፡ ይህም ማርቆስ አሁንም ለሚመጡት ነገሮች ደቀመዛሙርት በነበራቸው ዝግጅት ላይ ማርቆስ አፅንዖት የሰጠ መሆኑን እነድናይ ይረዳናል፡፡ ከዚህ ትንበያ በኋላ፣ እግዚአብሔር ሰው እንደሚፈርድ እንደማይፈርድ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ በማብራራት ማዘጋጀቱን ይቀጥላል፡፡ እናማ፣ የቱንም ህል መከራ ይቀበሉ፣ ምንም ያህል

እንግዳ ነገር ይድረስባቸው፣ ዓለም እንደምታይ እንዳያዩ ሳስባቸዋል፡፡ ይልቁኑ እግዚአብሔር እነዚያን ነገሮች መንግሥቱን ለማምጣትና ኢየሱስን ለማክበር እንደሚጠቀምባቸው እርግጠኛ ሊሆኑ ይገባል፡፡

ኢየሱስ በማርቆስ 9፥30-31 ስለ ራሱ አስቀድሞ ከተናገረ በኋላ፣ኢየሱስ በእግዚአብሔር መንግሥት እሴቶች ላይ ያስተማራውን ማርቆስ ይዘግባል፡፡ በዚህ ክፍል፣ የዓለማዊ ምኞት ከእግዚአብሔር እውነቶች ጋር ምን ያህል እንደሚጋጭ በአምስት የሕይወት አቅጣጫዎች ኢየሱስ ይገልጥልናል፡፡

በመጀመሪያ፣ በማርቆስ 9፥32-42 በእግዚአብሔር መንግሥት ከሁሉ የሚበልጡት በዚህ ዓለም ከሁሉ የሚያንሱት መሆናቸውን በማመልከት ኢየሱስ ስለ ከበሬታ ይናገራል፡፡

ሁለተኛ፣ በማርቆስ 9፥43-50 ውስጥ ኢየሱስ ስለ እርባና ይናገራል፡፡ በተለይም፣ ምንም ያህል በአሁኑ ሕይወት የከበሩ ቢመስሉም ተከታዮቹ የእግዚአብሔርን መንግሥት ግቦች ከመሻት ወደኋላ ከሚጎትቷቸው ነገሮች እንዲርቁ ያዛቸዋል፡፡

ሦስተኛ፣ በማርቆስ 10፥1-12 ኢየሱስ ስለ ጋብቻ ይናገራል፡፡ ነጥቡም ምንም እንኳን የሰው ህግ በጣም የሚመች ቢመስልም ጋብቻና ፍቺ ሊከናወኑ የሚገባቸው እንደ ሰው ስርዓት ሳይሆን እንደ እግዚአብሔር ህግ ሊሆን እንደሚገባ ማሳየት ነው፡፡

አራተኛ፣ በማርቆስ 10፥13-16 እንደገና ስለ ልጆች ይናገራል፡፡ ኢየሱስ ቀደም ብሎ ቢናገርም፣ ደቀመዛሙርቱ አሁንም ልጆች ወደ እርሱ እንዳይመጡ ይከለክላሉ፡፡ በምላሹም፣ ኢየሱስ እግዚአብሔር መንግሥቱን ለልጆች እንደሰጠ ያሳስባቸውና ልጆችን በመከልከላቸው ደቀመዛሙርቱ እግዚአብሔርን እየተቃወሙ እንደሆነ ይናገራል፡፡

አምስተኛ፣ በማርቆስ 10፥17-31 ኢየሱስ ስለ ብልጥግና ይናገራል፡፡ ይህም ስለ ጎልማሳው ባለጠጋ የሚናገረው የታወቀ ታሪክ ሲሆን፣ እርሱም ከገንዘብ ጋር ያለው ቁርኝት የእግዚአብሔርን መንግሥት እሴቶች የራሱ እንዳያደርግ እንቅፋት እንደሆኑበት ኢየሱስ ሲነግረው ተስፋ የቆረጠው ነው፡፡

በእያንዳንዳቸው በእነዚህ የትምህርት ክፍሎች፣ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት እሴቶች በማብራራት፣ ደቀመዛሙርቱ የእርሱን የመከራ ሞት ለመቀበል በተሻለ መንገድ ዝግጁ እንዲሆኑና እንደ እርሱ ተከታይነታቸውም በመከራዎቻቸው አንዲፀኑ ያሳስባቸዋል፡፡

ኢየሱስ ለኢየሩሳሌም ስላደረገው ዝግጅት የሚያወሳው ሦስተኛው የማርቆስ ወንጌል ክፍል ማርቆስ 10፥32-52 የሚያወሳው በእግዚአብሔር መንግሥት ስላለው አመራር ነው፡፡

ኢየሱስ በማርቆስ 10፥32-34 ስለ መከራው፣ ስለ ሞቱ እና ስለ ትንሣኤው አስቀድሞ ከተናገረ በኋላ፣ በመንግሥቱ ውስጥ ስላለው አመራር ለሚነሱ ጥያቄዎች በሦስት ክፍሎች መልስ ይሰጣል፡፡

በመጀመሪያ፣ ዮሐንስና ያዕቆብ የመከራው ተካፋዮች እንደሚሆኑ በማርቆስ 10፥35-40 ይናገራል፡፡ እርሱ የሚጠጣውን ጽዋ ይጠጣሉ በተመሳሳይም ጥምቀት ይጠመቃሉ፡፡ እነዚህ ተለዋጭ ዜቤዎች የኢየሱስ ተከታዮች እርሱን ከማገልገላቸው የተነሳ የመከራው ተካፋይ እንደሚሆኑ ያመለክታሉ፡፡

ሁለተኛ፣ በማርቆስ 10፥40-45 ውስጥ መሪነት በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ሎሌነት መሆኑን ኢየሱስ ያብራራል፡፡ ይህንንም ሃሳብ አስቀድሞ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት እሴቶች ሲናገር ሁለት ጊዜ

ጠቅሶታል፡፡ ከበስተኋላው ያለውን ምክንያት ሲናገር ግን ይህ የመጀመሪያ ነው፡፡ እርሱ ራሱ ስለ ኃጢአት መከራን በመቀበልና በመሞት እንደሎሌ ስላገለገለ፣ ክርስቲያን መሪዎችም የኢየሱስን ምሳሌነት በመከተል ሎሌዎች ሊሆኑ ይገባል፡፡

ሦስተኛ፣ ኢየሱስ የሎሌያዊ መሪነትን ተነሳስቶ የገለጠው ለዐይን-ስውሩ በርጠሜዎስ ምህረትን በማድረግ ነው፡፡ ሎሌያዊ መሪዎች መስዋዕትነት የሚከፍሉት በእግዚአብሔር መንግሥት ታላቅ ብድራት ለመቀበል ብቻ ሳይሆን፣ ስለሚያገለግሏቸው ሰዎች እውነተኛ ርኅራኄ ስላላቸው ነው፡፡

> ***ክርስቲያን መሪዎች ለህዝባቸው ሎሌ በመሆን የተለዩ እንዲሆኑ፣ ኢየሱሰ ጥሪ ያቀርብላቸዋል፡፡ በማርቆስ 10፥45 ውስጥ በሚገኘው በዚህ አስደናቂ ምንባብ፣ ኢየሡስ የእርሱ እውነተኛ ተከታዮች ሊከተሉት የሚገባውን የአመራር አይነት በወቅቱ በዙሪያቸው ከነበረው ግሪኮ-ሮማዊ ባህል ጋር በመለየት ያሳያል፡፡ በማርቆስ ዘመን ውስጥ ዕውቅ የነበረው የአመራር ዓይነት ሮማውያን በሕዝቡ ላይ ያሳዩት የነበረው የጭቆና አገዛዝ ነበር፡፡ እናም ኢየሱስ "እኔ ነፍሴን ለብዙዎች ቤዛ አድርጌ ልሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉኝ አልመጣሁም" ብሎ ተናገረ፡፡ ስለዚህም፣ ኢየሱስ፣ የእርሱ ተከታዮች የእርሱን ዓይነት የአመራር ዘይቤ እንዲከተሉ፣ እንደ ሎሌም እንዲመሩ እና በማርቆስ ዘመን የነበረውን የሮማውያንን የጭቆና አገዛዝ ዘይቤ እናዳይከተሉ ይጠይቃል ያዛልም፡፡ (ዶ/ር ግሬግ ፔሪ)***

በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ያለ አመራር በዓለም ውስጥ እንዳለው እንዳይሆን፣ ይልቁኑ የእርሱን የመከራ ተምሳሊት እንዲከተል ኢየሱስ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

በአንድ መንገድ፣ በሮም ለሚኖሩ የማርቆስ አንባቢዎች ልብን የሚሰብር ዜና ነው፡፡ እያለፉበት ያለው መከራ ተገቢ ያልሆነና ቶሎ የሚያልፍ መሆኑን ከመናገር ይልቅ፣ ኢየሱስን ለሚከተሉ መከራ አይቀሬ መሆኑን የማርቆስ ወንጌል ያስረግጥላቸዋል፡፡ ግን ደግሞ፣ ይህ ዜና የሚያበረታታም ነገር አለው፡፡ የቤተክርስቲያን መከራ ክርስቶስ ለድል ያቀደው ዕቅድ አካል ነው፡፡ ጳውሎስ በሮሜ 8፥18 እንደጻፈው ማለት ነው፡፡

> ***ለእኛም ይገለጥ ዘንድ ካለው ክብር ጋር ቢመዛዘን የአሁኑ ዘመን ሥቃይ ምንም እንዳይደለ አስባለሁ። (ሮሜ 8፥18)***

ማርቆስ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ስለ ማዘጋጀቱ ከዘገበልን በኋላ፣ በማርቆስ 11፥1-13፥37 ከአይሁድ መሪዎች ጋር ወደ ገጠመው ፍልሚያ ይሸጋገራል፡፡

## ፍልሚያ

ስለ ፍልሚያው የማርቆስ ዘገባ በሁለት ዋና ክፍሎች ይከፈላል፡ በመጀመሪያ፣ በ8፥31-12፥41 ያለው የተቃውሞ ትረካ እና በ13፥1-37 በደብረ ዘይት ተራራ ላይ ያደረገው ንግግር ናቸው፡፡

በዚህኛው የወንጌሉ ክፍል ውስጥ፣ ኢየሱስ የአይሁድ መሪዎች እጅ እንደሚቀሰቅስ ዓይነት አድርጎ ማርቆስ ዘግቧል፡፡ ቀደም ባሉት የማርቆስ ወንጌል ክፍሎች፣ ከአይሁድ መሪዎች ጋር መጋጨት አይፈልግም ነበር፤ ተቃውሞ ይገጥመው የነበረው፣ ሰዎች የምህረት አገልግሎቱን ሲቃወሙ ነበር፡፡ በዚህ ክፍል ግን፣ ኢየሱስ ወደ መስቀሉ የሚያደርገውን ጉዞ ለማፍጠን ኢየሱስ ተቃውሞውን በንቃት ሲጠብቀው ማርቆስ ይዘግብልናል፡፡

በመጀመሪያ፣ በማርቆስ 11፥1-11 ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም በድል በመግባቱ መሲህነቱና የእስራኤል ንጉሥ መሆኑ በአደባባይ ታወጀ፡፡

ቀጥሎ ደግሞ፣ በማርቆስ 11፥12-14 እስራኤልን እንደ ደረቀች የበለስ ዛፍ መርገሙእና ከቁጥር 15 -19 መቅደሱን ማንፃቱ፣ የአይሁድ መሪዎች በህዝቡ ዘንድ የነበራቸውን ተፅእኖ ያቀለለ ሲሆን ለዘመናት ያራምዱት የነበረውን የሞራል ደረጃም ጥቃት አድርሶበታል፡፡

ኢየሱስ በተጨማሪም፣ በማርቆስ 11፥27 - 12፥12 ውስጥ እንደምናየው ከካህናት አለቆች፣ ከህጉ መምህራን እና ከሽማግሌዎች ጋር ተከራክሯል፡፡ በሥልጣኑ ላይ ነበራቸውን ሙግት ከረታ በኋላ፣ የአይሁድ መሪዎች በእግዚአብሔር ላይ ስለ ማመፃቸው ስለሚናገረው ስለ ወይኑ ቦታ ጭሰኛ ገበሬዎች ታሪክ ነገራቸው፡፡ በዚህ ነጥብ ላይ፣ ሊያስሩት ዝግጁ ነበሩ፣ ሆኖም መንጋውን ስለ ፈሩ አላደረጉትም፡፡

ከዚያም፣ በማርቆስ 12፥13-17 ለሮማውያን ግብር ስለ መክፈል ፈሪሳውያንና ከሄሮድስ ወገን የሆኑት ያነሱትን ሙግት ውድቅ አደረገ፡፡

ከዚህ በኋላ፣ በማርቆስ 12፥18-27 ውስጥ፣ ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ ትንሣኤ የሚያስተምሩትን ሰዱቃውያን እንዴት እንደሳቱት አረጋገጠባቸው፡፡

በመጨረሻም፣ በማርቆስ 12፥28-44 የህጉን መምህራን አጥቅቷቸዋል፡፡ ምንም እንኳን አንዳንዶቹ ህጉን እንደሚያውቁ ኢየሱስ ቢቀበለውም፣ በጥቅሉ ግን በስግብግብነትና በዓለማዊ ምኞት የታነቁ መሆኑን አጋልጧል፡፡

በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ፣ ተፅዕኖ ፈጣሪ የሆኑ አይሁድውያንን በአደባባይ ተፋልሚቸዋል፡፡ እነርሱም፣ ካህናት፣ የህጉ መምህራን፣ ፈሪሳውያን እና የሄሮድስ ወገኖች እና ሰዱቃውያን ናቸው፡፡ እያንዳንዱ ቡድን እርሱን እንዲጠላ እና የሚሞትበትን መንገድ እንዲፈልግ፣ እንዲያውም እርሱን ሊገድሉ የሚችሉበትን መንገድ እንዲቀይሱ በሚያደርግ መንገድ ቀስቅሷቸዋል፡፡

ከአይሁድ መሪዎች ጋር ያደረገው ሁለተኛው ዐቢይ ክፍል በኢየሱስና በደቀመዛሙርቱ መካከል የነበረው ንግግር ነው፡፡ ይህ ንግግር የደብረዘይቱ ንግግር በመባል የሚታወቅ ስሆን ምክንያቱም በደብረዘይት ተራራ ላይ መደረጉ ነው፡፡ በማርቆስ 13፥1-37 በስፋት ተዘግቧል፡፡ በዚህ ክፍል፣ ደቀመዛሙርቱ ወደፊት ስለሚጠብቃቸው መከራ እና ወደ ፈተናም እንዳይገቡ ኢየሱስ ያስጠነቅቃቸዋል፡፡ ስለ እርሱ ለመመስከር በገዢዎች ፊት እንደሚቆሙ አስተምሯቸዋል፡፡ ይደበደባሉ፡፡ ይጠላሉ፡፡ ቤተሰባቸው ይበተናል፡፡ ተፈጥሯዊ መከራና ታላቅ ስደት ይገጥማቸዋል፡፡ እንዲያውም፣ እርሱ ተመልሶ እስኪመጣ ድረስ ቤተክርስቲያን በመከራና በስደት ውስጥ እንደምታልፍ ግልፅ ያደርግላቸዋል፡፡

ሆኖም ደግሞ በስተመጨረሻው የእግዚአብሔር መንግሥት ድል የምትነሳ መሆኗን በመግለጥ ለደቀመዛሙርቱ ታላቅ ተስፋን ይሰጣቸዋል፡፡ ለምሳሌ፣ በማርቆስ 13፥26-27 ውስጥ፣ መንግሥቱን በኃይልና በክብር ሲያመጣ ለእርሱ ታማኝ ሆነው እስከዘለቁ ድረስ ስለሚቀበሉት ድል ያሳስባቸዋል፡፡

ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ የተናገራቸው ቃላት የአይሁድን መሪዎች በእርሱ ላይ እንዲነሳሱ እንደሚደርጋቸው መተንበይ ይቻላል፡፡ ለምሳሌ፣ በማርቆስ 13፥1-2፣ መቅደሱ እንደሚደመሰስ ለደቀመዛሙርቱ ያስተምራቸዋል፡፡ በማርቆስ 14፥58 እንደምናነብበው ግን፣ ቃሎቹ በአግባቡ አልተደመጡም ሰውም አልተረዳቸውም፣ ስለዚህም መቅደሱን አፍርሰዋለሁ ብሏል ብለው በሃሰት ሊከሱት አቅደዋል፡፡

ማርቆስ የመሲሁን መከራ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ከማዘጋጀት አንፃርና ከአይሁድ መሪዎች ጋር በኢየሩሳሌም ከመፋለሙ አንፃር የዘገበውን ተመልክተናል፣ አሁን ደግሞ በማርቆስ 14፥1 - 15፥47 ወደተመዘገበው የኢየሱስ መከራና ሞት እንሻገራለን፡፡

**ልምምድ**

ኢየሱስ በመከራና በሞት ውስጥ ያለፈባቸው ጊዜያት በታወቁ ሁነቶች የተሞሉ ናቸው፡፡ እነርሱም፣ የይሁዳ አሳልፎ መስጠት፣ የጴጥሮስ መካዳት አስቀድሞ መነገሩ፣ በጌተሰማኒ ደቀመዛሙርቱ ከኢየሱስ ጋር ሊፀልዩና ነቅተው ሊጠብቁ አለመቻላቸው፣ የኢየሱስ መያዝ፣ ሁለቱ ሸንጎዎችና የጴጥሮስ መካዳት እናም በመጨረሻ የኢየሱስ መሰቀልና መቀበር ናቸው፡፡

እዚህም እጅግ የጨለሙና ፈታኝ ምዕራፎች ናቸው፡፡ በውድቀት የተሞሉ ናቸው ማለትም፡ በአይሁድ መሪዎች ከስረት፣ በህዝቡ ከስረት፣ በአይሁድና በሮማውያን የህግ ስርዓቶች እና በደቀ መዛሙርት ከስረቶች የተሞሉ ናቸው፡፡ ማርቆስ በስደት ላይ ላለችው ለሮም ቤተክርስቲያን ሲጽፍ፣ በኢየሩሳሌም የክርስትና የምጥ ጣር በሮም እንደነበረው ሁሉ እጅግ የከፋ መሆኑን ግልፅ እያደረገ ነበር፡፡

ስለ ኢየሱስ መከራና ሞት ማርቆስ የጻፈው ወንጌል በአራት ዋና ክፍሎች ይከፈላል፣ የሚጀምረውም ለሞቱ ስለ መቀባቱ በተጻፈው በማርቆስ 14፥1-11 ነው፡፡

በዚህ ክፍል፣ ማርቆስ ወሳኝ የሆኑ ዝርዝሮችን ይዘግብልናል፡፡ በመጀመሪያ፣ የካህናት አለቆችና የህጉ መምህራን ኢየሱስን የሚይዙበትንና የሚገድሉበትን መንገድ ይፈልጉ ነበር ይላል፡፡ ሁለተኛ፣ አንድ ሴት ኢየሱስን በጣም ውድ በሆነ ሽቱ ቀባችው፣ እርሱም ለቀብሩ ቀን እንደቀባቸው ተናገረ ይለናል፡፡ በዚህ መንገድ፣ ኢየሱስ በቶሎ እንደሚገደል አመልክቷል፡፡ ሦስተኛ፣ የአስቆሮቱ ይሁዳ ኢየሱስን ለካህናት አለቆችና ለህጉ መምህራን አሳልፎ ሊሰጥ ያሴራል፡፡ ይህንንም ስለ ኢየሱስ መከራና ሞት የተፃፈው ታሪክ አቅጣጫ የቀየረበት ስፍራ አድርገን እንወስደዋለን፡፡ የመሞቱ ጉዳይ እንዲያው ባዶ ስጋት ሳይሆን የማይቀር እውነታ መሆኑ ነው፡፡

ቀጥሎም፣ ማርቆስ ኢየሱስ ከደቀመዛሙርቱ ጋር ያሳለፉትን የመጨረሻ ሰዓት በማርቆስ 14፥12-42 ውስጥ ይዘግብልናል፡፡

በማርቆስ 14፥12-31 የተመዘገበው ይህ የማርቆስ ትረካ ክፍል የሚጀምረው ኢሱስና ደቀ መዛሙርቱ የመጨረሻዋን ራት ለመመገብ በሚያደርጉት ዝግጅት ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቲያኖች ሊጠብቁት የሚገባውን የጌታ ራት ስርዓት የደነገገው በዚህ ወቅት ነው፡፡ በተጨማሪም ደቀመዛሙርቱን በእርሱ የመጨረሻ መከራና ሞት ወቅት ውስጥ ሲያልፉ የሚጠቅማቸውን የዝግጅት ሃሳብም አንስቶበታል፡፡ ለምሳሌ፣ ሁሉም ከእርሱ እንደሚሸሹ፣ ጴጥሮስም እንደሚክደው ነግሯቸዋል፡፡

ከመጨረሻዋ ራት በኋላ፣ በማርቆስ 14፥32-52 እንደምንመለከተው ቡድኑ ወደ ጌተሰማኒ የአትክልት ስፍራ ሄዷል፡፡ በዚህ ምንባብ መሠረት፣ ኢየሱስ በብርቱ አዝኗል፣ ተጨንቋል እናም ነፍሱ እስከ ሞት ድረስ ተከዛለች፡፡ መስቀሉን እያሰበ በእጅጉ ተሰቃይቶ ነበር፡፡

ስለ ኢየሱስ መከራና ሞት ማርቆስ የጻፈው ወንጌል ሦስተኛ ክፍል በማርቆስ 14፥43-15፥15 የሚገኘው የኢሱስ መያዝና ወደ ሸንጎ መቅረብ ነው፡፡

ክፍሉ የሚጀምረው በደቀመዝሙሩ በይሁዳ ታልፎ ስለመሰጠቱ በማርቆስ 14፥43-52 በማውሳት ነው፡፡ በማርቆስ 14፥53-65 በአይሁድ መሪዎች ፊት ለፍርድ መቆሙ ደግሞ ይቀጥላል፡፡ ከዚያም፣ በማርቆስ 14፥66-72 ጴጥሮስ የኢየሱስ ተከታይ መሆኑ ሲታወቅበት ስለመካዳቱ የተጻፈውን እናነባለን፡፡ በመጨረሻም፣ በሮማው ገዢ በጲላጦስ ፊት ስለ መቅረቡ በማርቆስ 15፥1-15 ውስጥ እናነባለን፡፡ በዚህ ሁሉ ውርደት ማብቂያ ላይ፣ ኢየሱስ ተገረፈ፣ ይሰቀልም ዘንድ ለሮም ወታደሮች ታልፎ ተሰጠ፡፡

አራተኛውና የኢየሱስን መከራና ሞት መሰቀሉን ጨምሮ የሚተርከው የማርቆስ ዘገባ በማርቆስ 15፥16-47 ውስጥ ይገኛል፡፡

የመጀምረውም ኢየሱስ እንደ ተራ ወንጀለኛ ይደበደብ፣ ይዋረድ እና በመስቀል ላይ ይሞት ዘንድ ለሮማ ወታደሮች ታልፎ በመሰጠቱ ነው፡፡ ከሰብዓዊ ዕይታ አንፃር፣ መከራው አሰቃቂ ነው፡፡

ኢየሱስ በሮማውያን እጅ ይህንን የመሰለውን መከራ የመቀበሉ እውነታ የማርቆስ ተደራሲያን ከሆኑት የሮም ክርስቲያኖች ሁኔታ ጋር በብርቱ ይያያዛል፡ እነርሱ እያለፉበት ባለው መከራና የእነርሱ ጌታ ባለፈበት መካከል ያለውን ግንኙነት ፈጥነው ያስተውሉታል እናም በሚያልፉበት መከራ ውስጥ እርሱን እያሰቡ እንዲፀኑ ብርታት ይሆናቸዋል፡፡

ከኢየሱስ መከራዎች ሁሉ የከፋ የሚሆነው ግን የዓለሙ ሁሉ ኃጢአት በእርሱ ላይ መሆኑና በእግዚአብሔር ቁጣ ስር መውደቁ ነው፡፡ በመጨረሻም፣ ከሞተ በኋላ፣ በመቃብር ውስጥ ገባ፣ ሰውነቱ ግን ለቀብር የተዘጋጀ አልነበረም ምክንያቱም ሰንበት ከመግባቱ በፊት ይህን ለማድረግ የሚያስችል ምንም ጊዜ አልነበረምና፡፡

እንግዲህ የመሲሁን መታወጅ፣ የመሲሁን ኃይል፣ ስለ መሲሁ ሐዋርያት የሰጡትን ማረጋገጫ እና የመሲሁን መከራ ከተመለከትን፣ በማርቆስ 16፥1-8 ወደሚገኘው እና ማርቆስ ትንሣኤውን ወደገለጠበት የመሲሁ ድል እንሸጋገራለን፡፡

## የመሲሁ ድል

ወደዚህ ክፍል ይዘት ከመግባታችን አስቀድሞ፣ የማርቆስ ወንጌል የሚጠናቀቀው በ16፡8 ላይ ለምን እንደሆነ እናብራራ፡፡ መጽሐፍ ቅዱሶቻችን በዚህ ምዕራፍ ውስጥ 20 ቁጥሮችን ይዘዋል፡፡ ግን ደግሞ ከ9-20 ያሉት ቁጥሮች በማርቆስ ወንጌል በጥንታዊ ቅጂዎች ውስጥ እንደማይገኙ ማስታወሻ ይፅፋሉ፡፡

በጥንታዊው የማርቆስ ወንጌል ግሪክኛ ቅጂ ውስጥ፣ ሦስተ አጨራረሶች አሉ፡፡ አንዱ ቡድን በቁጥር 8 ይጠናቀቃል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ በቁጥር 20 ይተናቀቃል፡፡ ሦስተኛው ደግሞ ከቁጥር 8 በኋላ ሁለት የመዝጊያ ዐረፍተ-ነገሮችን ያስቀምጣል፡፡

ማርቆስ ወንጌሉን "**ፈርተው ነበርና**" በሚለው ሐረግ ዘግቶታል ብሎ ማመን ለፀሐፊው ምቾት ስላልሰጠው ሁለቱ ጠጨማሪ መደምደሚያዎች ተጨምረዋል የሚለውን ሃሳብ በርካታ ምሁራን ያምኑበታል፡፡ ሆኖም ይህ የፀፊ ስጋት ሊገኝ ግን አልቻለም፡፡ እንዲያውም፣ የፍርሃት፣ ግራ የመጋባትና የመደንገጥ ሃሳብ በወንጌላት ሁሉ ውስጥ የሚገኝ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት፣ ይህንን ወንጌል በፍርሃት ላይ አፅንዖት በመስጠት ማጠናቀቁ በጣም ተገቢ ነው፡፡ ደግሞም ከማርቆስ

ተደራሲያን ልምምድም ጋር በደንብ ይጋጠማል፡ ከኢየሱስ ትንሣኤ በኃላ በገጠማቸው ስደት፣ የኢየሱስ ቀደምት ደቀ መዛሙርትም ፍርሃት እንደነበረባቸው ማወቃቸው በእርግጥ ያፅናናቸዋል፡፡

አሁን በማርቆስ 16፥1-8 ወደሚገኘው የኢየሱስ ትንሣኤ እንለፍ፡፡ ማርቆስ የጻፈው የትንሣኤ ታሪክ ከሌሎቹ ወንጌላት ተመሳሳይ ታሪክ አጭር ነው፣ ይህ ደፋርነት ግን በማርቆስ አስተዋፅዖም ውስጥ የምናየው ባህርይ ነው፡፡ እንደምታስታውሱት፣ ወንጌሉ የተከፈተበት የመሲሁ አዋጅም እንዲሁ በጣም አጭር ነበር እንዲሁም የወንጌሉ ማዕከል የሆነው የሐዋርያቱ የመሲሁ ማረጋገጫም እንደዚያው ነበር፡፡

ይህ የመሲሁን ድል የሚያወሳው ታሪክ የሚጀምረው ከሞተና ከተቀበረ በኋላ ሰውነቱን ለመቀባት ወደ መቃብሩ ስለመጡ ሴቶች በማውሳት ነው፡፡ መልእክታቸው ቀጥተኛና ግልፅ የሆነ መላእክት አግኝተዋቸው ነበር፡፡ በአገልግሎቱ ዘመን ሁሉ አስቀድሞ ይናገር እንደነበረው ኢየሱስ ሞትን ድል አድርጎ ተነሥቷል፡፡ እስኪ የማርቆስ ወንጌል ማብቂያ የሆነውን በማርቆስ 16፥6-8 ያለውን አድምጡ፡-

> *እርሱ ግን፦ አትደንግጡ፤ የተሰቀለውን የናዝሬቱን ኢየሱስን ትፈልጋላችሁ፤ ተነሥቶአል፥ በዚህ የለም፤ እነሆ እርሱን ያኖሩበት ስፍራ።*
> *ነገር ግን ሄዳችሁ ለደቀ መዛሙርቱ ለጴጥሮስም፦ ወደ ገሊላ ይቀድማችኋል፤ እንደ ነገራችሁ በዚያ ታዩታላችሁ ብላችሁ ንገሩአቸው አላቸው።*
> *መንቀጥቀጥና መደንገጥ ይዞአቸው ነበርና ወጥተው ከመቃብር ሸሹ፤ ይፈሩ ነበርና ለማንም አንዳች አልነገሩም። እነርሱም ያዘዛቸውን ሁሉ ለጴጥሮስና ከእርሱ ጋር ላሉት በአጭሩ ተናገሩ። ከዚህም በኋላ ኢየሱስ ራሱ ለዘላለም ድኅነት የሆነውን የማይለወጠውን ቅዱስ ወንጌል ከፀሐይ መውጫ እስከ መጥለቂያው ድረስ በእጃቸው ላከው። (ማርቆስ 16፥6-8)*

እንደ ማርቆስ አተራረክ፣ የሴቶቹ ምላሽ የሚጠበቅ ነው፡ እጅግ ፈርተው ነበር፡፡ በዚህ ወንጌል ላይ የሚገኝ ሁሉም ሰው ማለት ይቻላል ለእግዚአብሔር ኃያል መገለጥ መልስ ይሰጥ የነበረው በአክብሮታዊ ፍርሃት፣ በመደነቅና በፍርሃት ነበር፡፡

> *ይህ የማርቆስ የተሰመረበት ዐረፍተነገር ነው፡፡ በዚህ ስፍራ ሴቶቹ ትንሣኤውን እንዲያውጁ ታዝዘዋል እነርሱ ግን ፈሩ እናም ከስፍራው ሮጡ ለማንም ምንም አልተናገሩም፡፡ ግን እኛም አሁን ከሁለት ሺህ ዓመታት በኋላም ይህንን ታሪክ ስናነብብ የታሪኩ መደምደሚያ ያ እንዳልሆነ እያወቅን፤ የእግዚአብሔር እውነት ድል መንሣቱንም እያወቅን፣ ነገሩ ግን ዛሬም በቅዱሳት መጻሕፍት ደጋግመን ያነው ሰብዓዊ ውድቀት ከእግዚአብሔር ታማኝነትና ዓላማ ጋር ያለው ተቃርኖ አሁንም እውን ሲሆን እናያለን፡፡ (ዶ/ር ሮበርት ፕላመር)*

የእግዚአብሔር ሰዎች በድካም ውስጥ ያልፋሉ ይህም የሕይወት አንዱ ክፍል ነው፡፡ ይህም በሮም ለሚገኙ ለማርቆስ ቀደምት ተደራሲያን እውነት ሲሆን፣ በየዘመናቱም ለምትገኘው ቤተክርስቲያን እውነት መሆኑ እንደቀጠለ ነው፡፡ ሆኖም የወንጌል ትልቁ የምሥራች ግን የእግዚአብሔር መንግሥት መምጣቷ ነው፡፡ መሲሁ የእግዚአብሔርን ህዝብ ጠላቶች፣ የመጨረሻውን ጠላት

ሞትን እንኳን ሳይቀር ድል አድርጓል፡፡ በዚህም ምክንያት፣ የእግዚአብሔር ህዝብ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወንጌል ጠላቶች በድፍረት ይጋፈጣሉ፡፡

የማርቆስን ወንጌል ዳራ፣ ውቅርና እና ይዘት ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ ዋና ዋና ሃሳቦቹን እንመለከታለን፡፡

# ዋና ዋና ሃሳቦች

ማርቆስ በወንጌሉ ኢየሱስን እንደ መሲህ ወይም እንደ ክርስቶስ የገለጠበት የማንነት መግለጫ አከራካሪ ሃሳብ ነው፡፡ ኢየሱስ የመጣው በእውነት ከኃጢአታቸው ሊያድናቸው መሆኑን አንባቢዎቹ እንዲያውቁ ማርቆስ ይፈልጋል፡፡ ኢየሱስ ሞትን ድል ያደረገ ንጉሥ ነው፡፡ እርሱ ኃያል፣ የተፈራ፣ ማንም ሊገታው የማይችል እና የከበረ ነው፡፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወደ ምድር በማምጣት ነፃ ሊያወጣቸው የመጣ ቤዛ ነው፡፡ ከእንግዲህ በዐይናቸው ሊያዩት ባይችሉም፣ እርሱ ግን ሁሉን ይገዛል ደግሞም የጀመረውን ድነት ሊፈፅመው ተመልሶ እንደሚመጣ ተስፋን ሰጥቷል፡፡

በዚህ ትምህርታችን ግን፣ የኢየሱስን መሲህነት በሁለት ክፍሎች እንከፍለዋለን፡፡ በመጀመሪያ፣ ኢየሱስን መከራን እንደሚቀበል መሲሃዊ አገልጋይ እንመለከተዋለን፡፡ ሁለተኛ ደግሞ፣ እንደ መሲሃዊ ድል አድራጊ ንጉሥ የተገለጠውን ማንቱን እንመለከታለን፡፡ እስኪ ኢየሱስ መከራን እንደሚቀበል አገልጋይ ያለውን ድርሻ በመመልከት እንጀምር፡፡

## መከራን የሚቀበል አገልጋይ

ኢየሱስን መከራን እንደሚቀበል አገልጋይ የምንመለከትበት ውይይታችን በሦስት ይከፈላል፡፡ በመጀመሪያ፣ መሲሁን አስመልክቶ አይሁድ ይጠብቁ የነበረውን እናነሳለን፡፡ ሁለተኛ፣ ኢየሱስ መከራን እንደሚቀበል አገልጋይ የገለጠውን የአገልግሎት ባህርይ እናሰምርበታለን፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ ስለ ኢየሱስ መሲህነት ይህን አመለካከት በመያዝ ማርቆስ አንባቢዎቹ ሊሰጡ ስለ ሚፈልገው ምላሽ እንነጋገራለን፡፡

በኢየሱስ ዘመን የተለመደ ስለነበረው አይሁድ ከመሲሁ ስለሚጠብቁት ነገር በመጀመሪያ እንልከት፡፡

## የአይሁድ ጥበቃ

ከክርስቶስ ዘመን መቶ ዓመታት ቀደም ብሎ፣ በርካታ አይሁዳውያን ከተስፋይቱ ምድር ውጪ ይኖሩ ነበር፡፡ በምድሪቱ ውስጥ ቀሩትም ደግሞ በአህዛብ ገዢዎች ጭቆና ይሰቃዩ ነበር፡፡ በመጀመሪያ ባቢሎናውያን ነበሩ፣ ከዚያም ሜዶንና ፋርስ፣ ከዚያም ግሪኮች፣ ከዚያም ሮማውያን ተቀባበሉዋቸው፡፡ ይህም የረጅም ዘመን የመከራ ታሪክ የአይሁድ የነገረ-መለኮት ሊቃውንት እግዚአብሔር በስተመጨረሻው የእስራኤልን መንግሥት ይመልስ ዘንድ መሲሃዊ ንጉሥ እንደሚልክ በብሉይ ኪዳን በተናገራቸው ትንቢቶች ላይ አፅንዖት እንዲሰጡ አድርጓቸዋል፡፡

የአይሁድ መሲሃዊ ተስፋዎች በርካታ ልዩ ልዩ ቅርፆች አሉት፡፡ ለምሳሌ፣ ቀናተኞቹ እስራኤል በመሲሁ ዘመን በሮሜ ባለሥልጣናት ላይ በማመጽ ያንን ድል ትቀዳጃለች ብለው ያምናሉ፡ የተለያዩ አቡቀለምሲሳዊ ቡድኖች ደግሞ እግዚአብሔር ራሱ በመለኮታዊ ጣልቃ ገብነት ጠላቶቹን በመደምሰስ ህዝቡን ያድሳል ብለው ያምናሉ፡፡ ፈሪሳውያንን የመሳሰሉት ደግሞ፣ እስራኤል ህጉን እስካልታዘዘች ድረስ እግዚአብሔር ጣልቃ አይገባም ብለው ያምኑ ነበር፡፡ እናም፣ በኢየሱስ ዘመን፣ መሲሃቸው እንዲመጣ የሚጠብቁ በርካታ ህዝብ ነበሩ ማለት ነው፡፡

እርሱ ግን እንደ ትሁት፣ መከራን እንደሚቀበል መሲህ መጣ፡፡ የአይሁዳውያኑ መሲሃዊ ተስፋዎች ይጠብቁ የነበረው ከብዙ ምዕተ-ዓመታት አስቀድሞ ዳዊት ይገዛበት እንደነበረው መንግሥት ዓይነት በመሲሁም ዘመን ያንኑ የሚመስል ፖለቲካዊ አስተዳደር የሚከተል ምድራዊ መንግሥት ይመጣል ብለው ነበር፡፡ ኢየሱስ ግን በምድራዊ የአግልግሎት ዘመኑ ይህንን የሚመስል መንግሥት ለመመሥረት እንኳን አልሞከረም፡፡ እናም ይህ ሁኔታ ብዙዎች እንደ መሲህ እንዳይቀበሉት አድርጓቸዋል፡፡

የሚገርመው ግን፣ መሲሁ መከራን የሚቀበል አገልጋይ የመሆኑ ሃሳብ ግን አዲስ አልነበረም፡፡ ነቢዩ ሲሳያስ በ53ኛው ምእራፉ ይህንን የመሲሁን ተግባር አመልክቷል፣ አዲስ ኪዳንም ይህንን በተደጋጋሚ ከኢየሱስ ጋር አገናኝቶታል፡፡ እንግዲያው ኢየሱስ መከራ በመቀበል ባያገለግል፣ ብሉይ ኪዳን ለመሲሁ ያስቀመጠውን መስፈርት አያሟላም ነበር ማለት እንችላለን፡፡ ስለዚህም፣ የኢየሱስ መከራን የመቀበል አገልግሎቱ ከክርስቶስነቱ ወድቅ ከማድረጉ ይልቅ በእውነትም ክርስቶስ የመሆኑ ማረጋገጫ ነው፡፡ በኢየሱስ ዘመን ግን ይህንን የብሉይ ኪዳን መሪ ሃሳብ የተረዱ በጣም ጥቂቶች ብቻ ናቸው፡፡ አብዛኞቹ ግን የዘመኑ አይሁዳውያን ከመሲሁ ይጠብቁ ለነበረው ቀቢፀ-ተስፋ ራሳቸውን ሰጡ ስለዚህም ሲመጣ እውቅና አልሰጡትም፡፡

> **በብሉይ ኪዳን ውስጥ የመሲሁ ሃሳብ እጅግ ወሳኝ ነገር መሆኑ ግልፅ ነበር፡፡ መሲሁ የተቀባው፣ የተቀባው ንጉሥ ነበር፡፡ ክርስቶስ የሚመጣው እንዴት ይሆን፣ ብሎ ግራ መጋባት ያስገርማል፣ እስራኤል ታዝዛ ቢሆንና ሰብዓዊ ንጉሥ ባትጠይቅ ኖሮስ? ግን ሁለቱንም ተላለፈች፡፡ እናም የእነዚህ ለህዝባቸው ግድ የማይላቸው "የተቀቡት" ዝርያ በቅደም ተከተል ቢመጣም፣ ራስ ተኮር ከመሆናቸው የተነሳ፣ በምድር የእግዚአብሔርን ፍትህ ሊያመጡ አልቻሉም፡፡ እናም ይህ ናፍቆት በብሉይ ኪዳን ይገለጥ ጀመር፡፡ ናፍቆቱም፣ "መሲሁ ሊያደርግ የሚገባውን የሚያደርግ አንድ መሲህ አናገኝ ይሆንን?" የሚል ነበር፡፡ የሚመጣው ንጉሥ ምን እንደሚመስል ከዚህ ትረዳላችሁ፣ በኢሳያስ ግን በሚመጣው ንጉሥና በመንፈስ ቅዱስ መካከል አስገራሚ ትስስር እንዳለ ትመለከታላችሁ፡፡ የብሉይ ኪዳን ሰዎች ይጠብቁ የነበረው መሲሁን ብቻ ሳይሆን፣ ቶራቸውን እንዲታዘዙ ያስችላቸው ዘንድ የመንፈስ ቅዱስንም መምጣት ይጠባበቁ ነበር፡፡ እናም በተለይም ኢሳያስ፣ በመሲሁና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ያለውን ግንኙነት እንዴት እንደሳለው ማየት የሚማርክ ነው፡፡ እርሱ በመንፈስ ቅዱስ ይሞላል፤ በመንፈስ የተቀባ ነው፡፡ እርሱ በመንፈስ ይናገራል፡፡ እናም ሐዋርያት ከሞት የተነሣው ኢየሱስ "አብ የሰጠውን ተስፋ በኢየሩሳሌም ጠብቁ" ሲላቸው አልገረማቸውም፡፡ ነገሩ የሚመስለው፣ "አሃ፣ በስተመጨረሻ መሲሁ እንዲናገር ስንጠብቀው የነበረውን ተናገረ፣**

***መንፈስ ቅዱስን እንዲመጣ አደርጋለሁ"*** እንዳለ ዓይነት ነው፡፡ ይህንን የእግዚአብሔርን የፍትህ እና የመንፈስ ቅዱስ ዘመን ለማምጣት መሲሁ ምን ዋጋ እንደሚያስከፍለው መረዳት ግን አቅቷቸው ነበር፡፡ ኢሳያስ 53 ከኢሳያስ 11 ጋር ማገናኘት አልቻሉም፡፡ መሲሁ ይህንን የፍትህ፣ የሰላም እና በመንፈስ የተሞላ ሕይወት ያዘለ መንግሥት ለማምጣት ሊሞት እንደሚገባው ማገናኘት አልቻሉም፡፡ (ዶ/ር ጆን አስዋልት)

ይህንን የአይሁድ ናፍቆት በልቡናችን ይዘን፣ ኢየሱስ መከራን እንደሚቀበል አገልጋይ ወደ ሰጠው አገልግሎት እንሸጋገር፡፡

## የኢየሱስ አገልግሎት

ኢየሱስ አስገራሚ መሲህ ነው ምክንያቱም ድል የነሳው በመሞት ነው፡፡ በወንጌሉ ጅማሬ ላይ፣ ግጭቶቹ በስተመጨረሻው ወደ ስቅለቱ ወስደውታል በማለት ማርቆስ ዘግቧል፡፡ የወንጌሉ ሁለተኛ ክፍል በመጀመሪያ በማይቀረው የኢሱስ መከራና ሞት ዙሪያ ኋላም በብርቱ መከራውና በሞቱ በራሱ ላይ ያጠነጠነ ነው፡፡

በኢየሱስ መከራ ላይ የተሰጠው ትኩረት በአገልግሎቱም ላይ ተሰጥቷል፡፡ እርሱ ብዙዎችን ፈውሷል አገልግሏቸዋልም፡፡ ኃጢአተኞችን ለመቤዠትም ነፍሱን ሰጥቷል፡፡ የእግዚአብሔርን ህዝብ ለመጥቀምም በሁሉም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ፈጽሟል፡፡

ይህን የመከራና የአገልግሎት ሃሳብ ማርቆስ በብርቱ ያገናኘበት ስፍራ ማርቆስ 10፥35-45 ያለው ነው፡፡ በዚህ ምንባብ፣ ያዕቆብና ዮሐንስ በመንግሥቱ የከበሬታን ስፍራ እንዲሰጣቸው ኢየሱስን ጠየቁ፡፡ የተቀሩት ደቀመዛሙርት ደግሞ ይህ የከበሬታ ስፍራ የመናፈቅ ጥያቄ አስቆጣቸው፡፡ አዪሱስ ግን ዐሥራ ሁለቱንም ገሰፃቸው፡፡ የአገልጋይነት ሕይወትንም እንዲናፍቁ አሳሰባቸው፣ የራሱንም ሕይወት በምሳሌነት አቀረበላቸው፡፡

> **አገልጋይ መሪነት መሪው በአገልጋይነት ሕይወት በንቃት እንዲሳተፍ እና ጳውሎስ እንደሚናገረውም፣ ሌሎችን ለማገልገል፣ ሌሎችን ለመደገፍ እና ለሎችን ለማብቃት ሕይወቱን እንዲያፈስስ ይጠብቅበታል፡፡ እናም መሪ በሉ ሂዱ ይህንን አድርጉ ብሎ የሚያዝዝ ብቻ አይደለም፡፡ አዎን፣ ትዕዛዙ ይሰጣል፣ መሪ ግን ዓላማዎቹንና ግቦቹን ለማሳካት የሚቻልበትን መንገድ ይመራል፡፡ ይህም ጳውሎስ በብርቱ ስለ መድከም የተናገረውን ያሳስበኛል፡፡ በዚህ ረገድ ከሁሉ ይልቅ ደከምሁ ብሎ ይናገራል፡፡ እናም ይህ ንግግሩ አገልጋይ መሪነት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ያሳያችኋል፣ ያም ዝቅ ብሎ የሰዎችን ሸክም ማገዝ እና ሊቤዥ በሚያስችል መንገድ መሸከምን ይጠይቃል፡፡ (ሬቨረንድ ላሬ ኮክሬል)**

እስኪ በማርቆስ 10፥45 ይህንን ስለመሰለው መሪነት ኢየሱስ የሰጠውን ማብራሪያ አድምጡ፡

> ***እንዲሁ የሰው ልጅም ሊያገለግልና ነፍሱን ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም። (ማርቆስ 10፥45)***

መሪነት እግዚአብሔርን እና የሚመራቸውን ሰዎች ማገልገል መሆኑን ኢየሱስ ግልፅ አድርጎታል፡፡ መሪነት የከበሬታ ዕድል አይደለም፡፡ በተቃራኒው ግን፣ መሪዎች በመከራ ውስጥ የሚያልፉበት ነው፡፡ እንዲያውም፣ ኢየሱስ ሌሎችን የማገልገል ተልእኮው በስተመጨረሻው ወደ ሞቱ እንደሚወስደው ያውቃል፡፡ ሆኖም እርሱ የሙጥኝ ያለው ተልዕኮው ይኸው ነበር፡፡ ደቀመዛሙርቱም እንዲይዙት የፈለገው ይህንኑ ተልእኮ ነበር፡፡

በማርቆስ ወንጌል ውስጥ፣ ኢየሱስ በብሉይ ኪዳን በትንቢት የተነገረለት መከራን የሚቀበለው መሲህ የመሆኑን መልእክት እንድናገኘው የጨከነ ይመስላል፡፡ በወንጌሉ የመጀመሪያ አጋማሽ፣ በኢየሱስ የንጉሥነት ሃላፊነቱ ላይ አፅንዖት ተሰጥቶበታል፣ በሁለተኛው አጋማሽ ደግሞወደ ኢየሱስ መከራና ሞት ተሸጋግረናል፡፡ እንዲያውም ቁልፉ ጥቅስ በማርቆስ 10፥45 *"የሰው ልጅም ሊያገለግልና ነፍሱን ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም።"* የሚለው ነበር፡፡ ይህ ጥቅስ የወጣው ደቀመዛሙርቱ ልክ በዚያ ሁኔታ ሊያገለግሉ እንደሚገባ በተነገረበት አውድ ውስጥ ሲሆን፣ ያም ስለ እግዚአብሔር መንግሥት መስፋፋትና ስለ ወንጌል ስንል መብቶቻችንን ሁሉ ወደ ጎን በማድረግ እንድናገለግል ኢየሱስ ተምሳሊታችን መሆኑ ነው፡፡ እናም ማርቆስ ተምሳሊቱን ማለትም ጌትነትን እንዳንፈልገው በመንግሥተ ሰማያትም የተመረጠውን ስፍራ ደቀመዛሙርቱ ያደርጉት እንደነበረው እንዳንፈልግ በእርግጥ አሳይቶናል፡፡ ይልቁኑ፣ ክርስቶስ ስለሌሎች ሲል ራሱን መስዋዕት እንዳደረገ ሁሉ፣ እኛም ልንከተለው የሚገባ ምሳሌ ያ መሆኑን አሳይቶናል፡፡ (ዶ/ር ሲሞን ቫይበርት)

ስለዚህም ይህ ኢየሱስ ያዘዘው ትዕዛዝ አገልጋይ መሪነት ማለት ምን ይመስላል ብለን የምናስብ ከሆነ፣ ያን የመሰለውን አመራር ኢየሱስ በወንጌል ውስጥ እንዴት እንደገለጠው እናያለን፡፡ ኢየሱስ ሲያደርግ ያየነው የመጀመሪያ ነገር ከተለያዩ ሰዎች ጋር ሲገናኝ መሻታቸውን አስመልክቶ በደንብ ያደምጣቸው ነበር፡፡ ባሉበትም ስፍራ ያገኛቸው ነበር፡፡ በሕይወታቸው ለሚፈልጓቸው ቁሳዊ መሻቶቻቸው፣ ለስሜታዊ መሻቶቻቸው ትኩረት ይሰጥ ነበር፤ ከቃሎቻቸው ባሻገር በቃል ያልተገለጡትን ሁሉ በእውነት ያደምጥ ነበር፡፡ ለምሳሌ በማርቆስ ወንጌል ውስጥ ይህንን የመሰለውን ነገር በአጋንንት ለረጅም ዓመታት ልጁ እየተሰቃየበት ካለው ማለትም ራሱን እየቆራረጠ፣ ከዚያ በኋላ ተስፋ ይኖረዋል ብሎ ከማያስብ አባት ጋር ሲነጋገር ተገልጦ እናገኘዋለን፡፡ ያለውም "አለማመኔን እርዳው" ነው፡፡ እርሱን ገለል እንዲልለት ከማድረግ ይልቅ፣ ኢየሱስ መልስ ሰጠው፣ ልጁንም ፈወሰው፡፡ እናም ከዚያ የወንጌሉን ግስጋሴ እንመለከታለን፣ ያም ኢየሱስ ወደየት ነው የሚሄደው? የሚለው ሲሆን ኢየሱስ የሚከተሉትን የኃጢአት ዕዳ ለመክፈል ነፍሱን ለመስጠት ወደ ኢየሩሳሌም እየሄደ ነበር፡፡ የዚህ የመስዋዕታዊ ፍቅር መግለጫ በዚያን ዘመን አስተሳሰብ ስለ ራስ ክብር የነበረውን ነገር ሁሉ ወዲያ የጣለና ነፍሱንም ስለሚከተሉት የሰጠበት ነበር፡፡ ኢየሱስ በወንጌል ያሰመረው መስመር ይህንን ይመስል ነበር፣ ስለሚያገኛቸው ሰዎች ግድ ይለዋል ያደምጣቸዋልም እናም ነፍሱንም ሊሰጥ ወደ ኢየሩሳሌም ይጓዛል፡፡ አገልጋይ መሪነት ማለትም ይህ ነው፡፡ (ዶ/ር ግሬግ ፔሪ)

አይሁድ ከመሲሁ ይጠብቁ ስለ ነበረው ነገርና ስለ አገልግሎቱ ያየነውን በልቡናችን ይዘን፣ ማርቆስ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ሲነግራቸው አንባቢዎቹ እንዲሰጡት ይጠብቅ የነበረውን ምላሽ እንመልከት፡፡

## ትክክለኛ ምላሽ

ተከታዮቹ መከራን ሊቀበሉ እንደሚገባ ኢየሱስ አስተምሯል፡፡ በማህበረሰቡ መካከል ተቃውሞ ይገጥማቸዋል፡፡ ከቤተሰቦቻቸው ጋር ይጋጫሉ፡፡ በአጋንንት ኃይላት ይፈተናሉ ይሰቃያሉም፡፡ ይሰደዳሉ፣ አንዳዶቹም ይገደላሉ፡፡ ይህም ሁሉ ሲሆን እነዲፀኑና በታማኝነት እንዲቆሙ ይጠብቅባቸዋል፡፡ በማርቆስ 12፥30 ኢየሱስ እንዴት እንዳጠቃለለው አድምጡ፡

> ***አንተም በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም አሳብህ በፍጹምም ኃይልህ ጌታ አምላክህን ውደድ የምትል ናት። ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት። (ማር 12፥30)***

በዚህ ስፍራ፣ ኢየሱስ ያጣቀሰው ከዘዳግም 6፥5 ሲሆን በህዝቡ ሕይወት ውስጥ እግዚአብሔር የሚፈልገውን ፍፁም መሰጠት አጽንዖት ሰጥቶበታል፡፡ በሁለንተናዊ ማንነታችንና በሕይወታችን ለእግዚአብሔር የተሰጠን ልንሆን ይገባናል፡፡

ኢየሱስን መከተል መስዋዕትነትና መከራም አለበት፡፡ ለእርሱ ሙሉ በሙሉ የተሰጠን ልንሆንም ይጠበቅብናል ደግሞም ስለ መንግሥቱ ስንል ዓለም እስክታንቋሽሽን ድረስ ለእርሱ ለመኖር ፈቃደኛ ልንሆን ይገባናል፡፡

አንድ ምሳሌ ለማንሳት፣ በማርቆስ 10፥17-31 ስለ ወጣቱ ባለጠጋ ገዢ የተፃፈውን እንመልከት፡፡ የዘላለምን ሕይወት እንዳገኝ ምን ማድረግ ይገባኛል በማለት ኢየሱስን ሊጠይቀው መጣ፣ ኢየሱስም ያለውን ሁሉ ሸጦ ለድሆች እንዲሰጥ ነገረው፡፡ ኢየሱስ የጠየቀው ጥያቄ ግን ወጣቱ ባለጠጋ ገዢ ሊሸከመው ከሚችለው በላይ ነበረና እያዘነ ሄደ፡፡ ይህም ደቀመዛሙርቱን እንዳያስገርማቸው ለደቀመዛሙርቱ ነገራቸው ምክንያቱም “**ባለጠጋ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ብትሾልክ ይቀልላልና፡፡**” ከዚያም በመቀጠል ተከታዮቹ ወላጆቻቸውን፣ ቤታቸውን እና ያላቸውን ሁሉ ሊተዉ እንደሚገባ ነገራቸው፡፡ ለመሰደድ ፈቃደኛ ሊሆኑ ይገባ ነበር፡፡ ስለ እርሱም ሊሰዉ ይገባ ነበር፡፡ ኢየሱስ በማርቆስ 8፥34-35 እንዲህ ብሏል፡፡

> **ሕዝቡንም ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ጠርቶ እንዲህ አላቸው፡- በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር፥ ራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ።**
> **ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታልና፥ ስለ እኔና ስለ ወንጌል ነፍሱን የሚያጠፋ ሁሉ ግን ያድናታል። (ማር 8፥34-35)**

በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ ክርስቲያን ሁሉ መስቀል አለው፡፡ የድነት ክብርና በረከት ግን መስዋእት ሊኮንለት ይገባል፡፡

በአንድ በኩል፣ ኢየሱስ መስቀልህን ያዝ ይላል፣ በጴጥሮስ ሕይወት ውስጥ ግን አንዳንድ ጊዜ በእጁ ውስጥ ከመስቀል ይልቅ ሰይፍ ይዞ ያየዋል። የሊቀካህናቱንም ጆሮ ይቆርጣል። አያችሁ፣ ለዘመናት በቤተክርስቲያን ግራ የሚያጋባ ነገር የሆነው ይኸው ነው፣ ሰይፍ ወይስ መስቀል? የሰዎችን ብልጣብልጥነት ወይስ የሰዎችን ዘዴ ወይስ የሰዎችን ጥበብ እንከተላለንን? ወይስ ራሳችንን በመካድ ለራሳችን ሞተን ኢየሱስን እንከተላለን? ያ ክብር፣ እግዚአብሔር በልጁ በኩል የሰጠው ክብር፣ የሚገኘው የመስቀሉን መንገድ፣ ኢየሱስ የሄደበትን መንገድ በመከተል ብቻ የሚገኝ ነው። ስለዚህ ጥያቄው እንዴት እናመቻምች፣ የት እናመቻምች ሳይሆን፣ በእውነት ኢየሱስን እንከተላለን ወይ? የሚል ነው። እናም ሰዎች ለዚያ ዓላማ ራሳቸውን ሲሰጡ፣ የኢየሱስም መንገድ የመስቀል መንገድ መሆኑን ሲረዱ፣ እርሱን መከተል ማለትም ለራስ መሞትና ለእርሱ መኖር መሆኑን ሲያውቁ፣ እነዚህ የማመቻመችና ያለማመቻመች፣ የአንድነትና የመበታተን ጥቄዎች በክርስትና ሕይወት ቅርፀ መስቀል ባህርይ ላይ እስካተኮርን ድረስ ራሳቸው በራሳቸው ምላሽ እያገኙ ይሄዳሉ። (ቄስ ሚካኤል ጉሎዶ)

ደቀመዝሙርነት የተለየ መንገድ ነው። በመሠረቱ፣ እንደ ኢየሱስ አባባል፣ በራሳችን ኃይል በመታመን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት የማይቻል ነው። ሆኖም በማርቆስ 10፥27 ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን እንዴት እንዳበረታታቸው አድምጡ፡

*ይህ በእግዚአብሔር ዘንድ እንጂ በሰው ዘንድ አይቻልም፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ሁሉ ይቻላልና አለ። (ማር 10፥27)*

እርሱ በሚፈልገው ፍፁም መንገድ ኢየሱስን መታዘዝ የምንችልበት ኃይል የለንም። እግዚአብሔር ግን ይችላል። እኛም ወደ መንግሥቱ መግባታችንን እርግጠኛ ለማድረግ በእኛ ውስጥ ያስቀመጠውን ኃይሉን ይጠቀማል።

ከምናደርጋቸው የከፉ ነገሮች አንዱ ያለ መንፈስ ቅዱስ ኃይል በክርስቶስ ለማደግ፣ ለመቀደስ፣ በቅድስናና በጽድቅ ለማደግ መሞከራችን ነው። ያ እግዚአብሔርን ደስ አያሰኘውም፣ ባዳነንና በእውነቱም በሚቀድሰን በእግዚአብሔር መደገፍም አይደለም። ስለዚህም፣ ከእኛ ሕይወት ለሚወጣ መልካም ነገር ሁሉና በሕይወታችን ለሚታይ እድገት በጠቅላላ፣ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ እና የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ፍጹም ወሳኝ ነው። አስደናቂው ነገር፣ በሰውነቱ ኢየሱስ ምሳሌያችን ስለሆነ፣ በእርሱ ሕይወት የምንመከተው ያን ነው። መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ ሕይወት ይመጣና ይሠራ ነበር፣ ያስችለው፣ ኃይልን ይሰጠው፣ ይመራው፣ በአገልግሎቱ መጀመሪያም ሲጠመቅ ይቀባው፣ እንዲያውም ከዚያ ቀደም ብሎም ከድንግል ሲፀነስና እግዚአብሔር ሰው እንዲሆን ሲያደርግም ነበር። ይፈተንም ዘንድ ወደ ምድረበዳ መንፈስ ሲወስደውም እናያለን። መንፈስ ይመጣና ያገለግለው ነበር። መንፈስ በክርስቶስ ሕይወት ውስጥ የማስቻልን ሥራ ይሠራ ነበር። እናም በእርግጠኝነት በክርስቶስ ተከታዮች ሕይወትም ውስጥ የማስቻሉን ሥራ የሚሠራው እርሱ ነው። (ዶ/ር ኬ. ኤሪክ ቶኔስ)

በሮም የሚኖሩ ተደራሲያኑ መከራቸውና ስደታቸው የኢየሱስ እውነተኛ ተከታዮች የመሆናቸው ምልክት መሆኑን እንዲያውቁ ማርቆስ ይፈልጋል። ይህም ኢየሱስ ለመንግሥቱ ያለው ዕቅድ አካል ነው። አንባቢዎቹም በዚህ እውነታ እንዲበረታቱ ማርቆስ ይፈልጋል። በመከራዎቻቸው ሁሉ

ውስጥ እንዲፀኑ እግዚአብሔር ኃይልን እንደሚሰጣቸው እንዲተማመኑ ይፈልጋል፣ ኢየሱስን እንዳበረታው ሁሉ፣ መከራዎቻቸውን በብርታትና በተስፋ ሊጋፈጡ ይገባቸዋል፡፡

ዛሬም ቢሆን ኢየሱስ መንግሥቱን ቀስ በቀስ እያመጣ ነው፤ የሕዝቡንም መከራ ወደ ዚያ ፍፃሜ የመድረሻ መንገድ ያደርገዋል፤ ዛሬም እርሱ እንድንፀና ያስችለናል፡፡ ስለ ኢየሱስ እና ስለ መንግሥቱ መከራ መቀበላችን ተስፋ ሊያስቆርጠን ዐይገባም፤ ይልቁኑ ሊያፅናናንና ሊያበረታን ይገባል፡፡ መከራ የምንቀበለው አገልጋዮቹ ስለሆንን ነው፡፡ አንድ ቀንም መከራችን በቃል ሊነገር ከሚችለው በላይ ብድራትን እንደሚያስገኝልን እናውቃለን ያም ፀንተን ያለፍንበትን መከራ ከማስረሳትም እጅግ የዘለሉ በረከቶች ያሉበት ነው፡፡

ስለ ኢየሱስ ማንነት የምናነሳው ሁለተኛው ክፍል የእግዚአብሔርን መንግሥት ወደ ምድር ያመጣው የድል አድራጊ ንጉሥነት ሃላፊነቱ ነው፡፡

## ድል አድራጊው ንጉሥ

መሲሁ የንጉሥ ዳዊት ዝርያ እንደሚሆን ብሉይ ኪዳን በግልፅ ያስቀምጠዋል፣ እናም የእርሱ ሥራ የደዊትን ዙፋን ማደስና በእስራኤልም ላይ ለዘላለም ገዢ መሆን ነው፡፡ ይህም በመዝሙር 89፣ 110 እና 132 ተተንብዮ፣ በማርቆስ 12፥35 ደግሞ ተረጋግጦ እናገኘዋለን፡፡ ስለዚህም፣ ኢየሱስ ከክርስቶስ ወይም ከመሲሁ ጋር ተገናኝቶ ስናገኘው፣ የእርሱ ንጉሣዊ ደረጃወ ተረጋግጧል ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ፣ በማርቆስ 10፥47-48 የዳዊት ልጅ ተብሎ የተጠራው ለዚህ ነው፡፡ ኢየሱስ ራሱም በማርቆስ 14፥61-62 ውስጥ በሸንጉው ፊት ለፍርድ በቀረበ ጊዜና በማርቆስ 15፥2 በጲላጦስ ፊት በቀረበበት ወቅት በግልፅ መሲሁ ንጉሥ መሆኑን አረጋግጧል፡፡

ማርቆስ ኢሱስን እንደ ድል አድራጊ ንጉሥ አፅንዖት የሰጠባቸውን ሦስት የሃላፊነት ገፅታዎችን እንረምራለን፡፡ ኢየሱስ መንግሥቱን የማወጁን እውነታ እናያለን፡፡ ኃይሉንና ሥልጣኑን መግለጡን እንመለከታለን፡፡ ደግሞም ጠላቶቹን ድል ማድረጉን ልብ እንላለን፡፡ እስኪ ኢየሱስ መንግሥቱን ያወጀ በመሆኑ እንጀምር፡፡

### የታወጀው መንግሥት

ማርቆስ እንዲህ በማለት ስለ ኢሱስ የወንጌል አገልግሎት ጠቅለል ያለ ዘገባ ያቀረበበትን መንገድ በማርቆስ 1፥14-15 ውስጥ እንመልከት፡

> **ዮሐንስም አልፎ ከተሰጠ በኋላ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወንጌል እየሰበከና። ዘመኑ ተፈጸመ የእግዚአብሔርም መንግሥት ቀርባለች ንስሐ ግቡ በወንጌልም እመኑ እያለ ወደ ገሊላ መጣ። (ማር 1፥14-15)**

የኢየሱስ የስብከት አገልግሎት ዓላማ የእግዚአብሔር መንግሥት ቅርብ መሆኗን የሚናገረውን ወንጌል ወይንም የምሥራች ማወጅና በረከቷም ንስሓ ለሚገቡና ለሚያምኑ እንደሚሰጥ ማብሰር ነበር፡፡

ኢየሱስ በተጨማሪም መንግሥቱን ያወጀው ምሥጢሯን ለደቀመዛሙርቱ በማስተማር ነው። እንዲያውም፣ በተደጋጋሚ ጊዜ በምሳሌዎቹ የመንግሥቱን ምሥጢር ለተመረጡት መግለጥ፣ ካላመኑት ግን መሰወር አስፈላጊ መሆኑን ያስተምር ነበር። እስኪ ኢየሱስ በማርቆስ 4፥11-12 ለደቀመዛሙርቱ የነገራቸውን እናድምጥ፡-

***እንዲህም አላቸው፡- ለእናንተ የእግዚአብሔርን መንግሥት ምሥጢር ማወቅ ተሰጥቶአችኋል፤ በውጭ ላሉት ግን፥ አይተው እንዲያዩ እንዳይመለከቱም፥ ሰምተውም እንዲሰሙ እንዳያስተውሉም፥ እንዳይመለሱ ኃጢአታቸውም እንዳይሰረይላቸው ነገር ሁሉ በምሳሌ ይሆንባቸዋል። (ማር 4፥11-12)***

በእርግጥም፣ ኢየሱስ ደጋግሞ የእግዚአብሔርን መንግሥት ይገልጥ ነበር። ለምሳሌ በማርቆስ 10 ህፃናት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በቀላሉ እንደሚገቡ፣ ባለጠጎች ግን በብዙ ጭንቅ እንደሚገቡ ይናገር ነበር።

ኢየሱስን እንደ ድል አድራጊው ንጉሥ የምንገልጥበት ሁለተኛው ገፅታ እንደ ምድራዊ የእግዚአብሔር መንግሥት የበላይ ባለሥልጣን የገለጠውን ኃይሉንና ሥልጣኑን መጥቀስ ነው።

## የተገለጠው ኃይልና ሥልጣን

ኢየሱስ በተቀዳሚነት ንጉሣዊ ኃይሉንና ሥልጣኑን የገለጠው በተዓምራቶቹ ነው። ለምሳሌ፣ ማር 4፥41 ፍጥረት ይታዘዘዋል ይላል። እንደ ማርቆስ 1፥24፣ 3፥11፣ እና 5፥7 የመሳሰሉትን ስንመለከት አጋንንቶች የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ያውቁ እንደነበር ያሳዩናል። ኢየሱስ በተፈጥሮና በአጋንንት ላይ ሥልጣኑን መግለጡ የእግዚአብሔርን መንግሥት በምድር ለማምጣት የመጣ የመሆኑ ጠንካራ መግለጫ ነው። ተዓምራዊ ፈውሶቹንም አስመልክቶ ነገሩ እንደዚያው እውነት ነው። የመንግሥቱ በረከቶች ሕይወትንና ጤናን ያካትታሉ። ስለዚህ፣ ኢየሱስ ሰዎችን ፈውሷል፣ የመንግሥቱንም በረከቶች እነደ መንግሥቱ ፈቃድ አድሏቸዋል።

**ኢየሱስ ተዓምራትን ያደረገው ምናልባት ቢያንስ ለሦስት ምክንያቶች ሊሆን ይችላል፡ አንዱ ርኅራኄውን ለማሳየት፣ እግዚአብሔር ለተጨነቁት ስላለው ርኅራኄ ማለት ነው። ሰዎችን የሚፈውሰው ርኅራኄው ግድ ስለሚለው እና ለእነርሱ ስለሚያዝን ነው። መሻታቸውን ሊያሟላ ይፈልጋል፣ ግን ያንን በማድረጉ ደግሞ፣ እርሱ ማን የመሆኑን እውነታ ያስተዋውቃል፣ ማለትም እርሱ የመዳንን መንግሥት የሚያመጣ መሲህ መሆኑን ማለት ነው። እናም ተዓምራቱ የማንነቱ ማስታወቂያዎች ናቸው፣ እንጂ እንዲያው አምላክ መሆኑንና እነዚያን ነገሮች የማድረግ አቅም ያለው መሆኑን መግለጫዎች ብቻ አይደሉም፣ መሲህነቱንም ያመለክታሉ። ሦስተኛው ገፅታ ደግሞ ተዓምራቱ መሲሃዊ ድነት መምጣቱን ያሳያሉ። እግዚአብሔር ተስፋ የሰጠበት ዘመን እነሆ በታሪክ ውስጥ ተገለጠ እናም አሁን በሽታ ያመጣብን መርገም ተንከባልሎልናል፣ እርሱም ሰዎችን እየፈወሰ ነው። እርሱ ምግብንና መጠጥንም አትረፍርፎ በመስጠት የምግብንና የመጠጥን እጥረት እያስወገደ ነው፣ ተዓምራቱም እግዚአብሔር ታሪክን እየለወጠ መሆኑን እና ለዚህም ምክንያቱ እርሱ መሲህ**

*መሆኑና ተልዕኮውም እነዚህን በረከቶች በሕይወታችን ማምጣት መሆኑ ነው፡፡ (ዶ/ር ጆን ማኪንሌይ)*

ተዓምራትን ከማድረጉ ባሻገር፣ ኢየሱስ ንጉሣዊ ሥልጣኑን በሌሎችም መንገዶች ገልጧል፡፡ ለአብነት ብናሳ፣ በማርቆስ 1፥16-20፣ ደቀመዛሙርቱ ቤታቸውን፣ ቤተሰባቸውንና ሥራቸውን ሁሉ በመተው እንዲከተሉት በግልፅ ጥሪ አድርጎላቸዋል፡፡ አንዲው ጥበብ የሞላባቸውን ምክሮች ብቻ አልለገሳቸውም፤ ይልቁኑ ሕይወት ለዋጭ ምላሽ ይተብቅባቸው ነበር፡፡ እንዲያውም፣ ወንጌልን ከሰሙ ሁሉ ያዘዘው ይህንኑ ሲሆን፣ ተመሳሳይ ምላሽም ይጠብቃል፡፡ የሰው ዘር ሁሉ ኢየሱስን የመታዘዝ፣ ሕይወታቸውን ለእርሱ የመስጠት እና እርሱ ወደ መራቸው ሁሉ እርሱን የመከተል ግዳጅ አለበት፡፡

ጨርሶ የማይዘነጋው የኢየሱስ ሥልጣን ተምሳሊት የተገለጠው በማርቆስ 2፥3-12 የሽባውን ሰው ኃጢአት ይቅር ባለበት ወቅት ነው፡፡ ኢየሱስና ሰዎች ሁሉ ኃጢአትን ይቅር የሚል እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ ያውቃሉ፡፡ በአስገራሚ ሁኔታ ግን፣ ሰውየው ይቅርታን ከእግዚአብሔር እንዲጠይቅ አልነገረውም፤ ይልቁኑ በሥልጣን ኃጢአቱን ይቅር አለው፡፡ በውጤቱም፣ ይህ አባባል ሰውየው ይቅር መባሉን ያረጋገጠ ብቻ ሳይሆን፣ የኢሱስንም ንጉዊ ሥልጣን አሳይቷል፡፡ የሰውየውን ኃጢአት ይቅር በማለት፣ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ሥልጣን ያለው መሆኑንም ኢየሱስ ገልጧል፡፡ ይቅር ካለው በኋላም ወዲያውኑ በመፈወስ፣ መልእክቱ በእውነት ከእግዚአብሔር የመጣ መሆኑን ኢየሱስ አረጋግጧል፡፡

በእርግጥም፣ የኢየሱስ ኃጢአትን ይቅር የማለት ሥልጣኑ እርሱን ልንከተል የሚገባ መሆኑን ከሚያሳዩ ትልልቅ ምክንያቶች የሚልቀው ነው፡፡ በእርሱ አማካይነት ኃጢአታችን ተወግዷል፣ ስለዚህም ከእግዚአብሔር ጋር ታርቀናል፡፡ ጠላቶቹ መሆናችን ቀርቶ፣ ከእርሱ ከምናገኛቸው ዘላለማዊ በረከቶች ጋር የመንግሥቱ ታማኝ ዜጎች ሆነናል፡፡

ቀጥለን የምንገልፀው የኢየሱስ ድል አድራጊ ንጉሥነት ሦስተኛ ገፅታ ጠላቶቹን ድል መንሳቱ ነው፡፡

## ጠላቶችን ድል መንሳት

ኢየሱስ በሕይወት ዘመኑ በርካታ ጠላቶች ነበሩት፡ ይቃወሙት የነበሩ የአይሁድ መሪዎች፣ የማይቀበሉትና የሚንቁት፣ ያስወጣቸው አጋንንቶች እና ሌሎችም ጠላቶች ነበሩት፡፡ ከጠላቶቹ ጋር በተጋፈጠባቸው ጊዜ ሁሉ ድል ያደርግ ነበር፡፡ ክርክራቸውን ያሸንፋል፤ ሴራቸውን አውቆ ገለል ይላል፤ ሰዎችንም ከጭቆና ነፃ ያወጣል፡፡ እንዲያውም ሴራቸውን የእርሱን ዓላማ ለማስፈፀሚያ በመጠቀም፣ የኃጢአት ማስተሰረያ ይሆን ዘንድ በመስቀል እንዲሰቅሉት ይተዋቸዋል፡፡ እነዚህ ሁሉ ድሎች ኢየሱስ በእውነት መሲህ፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወደ ምድር የሚያመጣ ከዳዊት ዘር የሆነ ንጉሥ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡

ማርቆስ ከጠቀሳቸው ጠላቶቹ መካከል አንዱ ጎራ አጋንንቶች ናቸው፡፡ እንዲያውም፣ ከሌሎቹ ወንጌላት ይልቅ ማርቆስ ኢየሱስ በአጋንንት እና በሰይጣን ላይ ያለውን ኃይል ጠንካራ አፅንዖት

ሰጥቶበታል፡፡ ተደራሲያኑ ኢየሱስ አጋንንትን የሚገዛ በመሆኑ ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ ማርቆስ ፈልጓል፡፡

ለማርቆስ፣ ኢየሱስ ከአጋንንት ጋር ያደረገው ፍልሚያ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ያመጣ የመሆኑ ማስረጃ ነው፡፡ የመንግሥቱ መምጣት ትግል የሌለበትን ሰላማዊ ኖሮ አያመለክትም፡፡ በተቃራኒው ግን፣ የኢየሱስ መንግሥት የመጣችው ከክፉው መንግሥት አጋንንታዊ ኃይላት ጋር ለመፋለምና በስተመጨረሻውም ድል ለመንሳት ነው፡፡ በሮም ለሚገኙ ክርስቲያኖች፣ መከራቸው የታላቁ መንፈሳዊ ጦርነት አካል ነው የሚል ፍቺ ይሰጣቸዋል፡፡

ምንም እንኳን ለጊዜው ቢሰደዱና ተቃውሞ ቢደርስባቸውም፣ ድል ግን ከእነርሱ ወገን ነው፣ እናም አንድ ቀን የፍፃሜውን ድል ይቀዳጃሉ፡፡ ለእኛም ነገሩ እንዲሁ እውነት ነው፡፡

የኢየሱስ ኃይል በአጋንንት ላይ አስደናቂ የመሆኑን ያህል፣ የእርሱ ትልቅ ድል ግን ጳውሎስ 1ኛ ቆሮንቶስ 15፥26 ውስጥ "**የመጨረሻው ጠላት**" ብሎ በጠራው በሞት በራሱ ላይ ነው፡፡ እንደተመለከትነው፣ ሞቱ ወደ ድል የመድረሻ መንገዱ መሆኑን ኢየሱስ ከመሞቱ አስቀድሞ ለደቀመዛሙርቱ ደጋግሞ አብራርቶላቸዋል፡፡ ሞት ጠላት ነበር፡፡ ኢየሱስ ግን ይህንን ጠላት ለራሱ ዓላማ ድል ይነሣል፡፡ አንድ ምሳሌ ለመጥቀስ፣ በመጨረሻው ራት ወቅት በማርቆስ 14፥24-25 ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ እንዴት እንዳረጋገጠላቸው እስኪ አድምጡ፡

> **እርሱም፦ ይህ ስለ ብዙዎች የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ነው። እውነት እላችኋለሁ፥ በእግዚአብሔር መንግሥት ከወይኑ ፍሬ አዲሱን እስከምጠጣበት እስከዚያ ቀን ድረስ ደግሞ አልጠጣውም አላቸው።**
> **(ማር 14፥24-25)**

እንደ ደግ እረኛ፣ ሞቱ የተስፋ መቁረጥ ምክንያት ሳይሆን፣ በኃጢአትና በጣጣዎቹ ላይ ድል የሚቀዳጅበት የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን እንደሚሆን ኢየሱስ ተስፋ ሰጥቷል፡፡ ኢየሱስ በተጨማሪም ይህ ከደቀመዛሙርቱ ጋር የሚበላው የመጨረሻ ራት እንዳልሆነም ተስፋን ሰጥቷል፡፡ አሁን ሊሆኑ ካሉት ከመያዙ፣ ለፍርድ ከመቅረቡ፣ መከራን ከመቀበሉ እና ከሞቱ በኋላ መንግሥቱ በፍፃሜው ወደ ሙሉ ክብሯ ስትመጣ እንደገና ከደቀመዛሙርቱ ጋር እንደሚጠጣ ተናግሯል፡፡ በጥንቱ ዓለም ከነበሩት ከማርቆስ ተደራሲያን አንስቶ በየዘመናቱ በተነሳችው ቤተክርስቲያን ውስጥም፣ የምንካፈለው የጌታ ራት የክርስቶስ ድል በስተመጨረሻው መከራዎቻችንን ሁሉ እንደሚያሸንፍ ያስታውሰናል፡፡ አንድ ቀን፣ ከኢየሱስ ጋር በአንድ ማዕድ ተቀምጠን ድላችንን እናከብራለን፡፡

ኢየሱስ በመሰቀሉ፣ በሞቱና በመቀበሩ ለጊዜው ሞት በእርሱ ላይ ኃይል እንዲኖረው ፈቅዶለታል፡፡ ስለዚህም እኛን ከኃጢአት ሊቤዥን ችሏል፡፡ ሆኖም ግን በሞት ኃይል ስር ሆኖ አልቀረም፡፡ በትንሣኤው፣ ሞትንም ድል በመንሣት፣ እርሱ ክርስቶስ፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት በምድር እንዲያመጣ የተላከ የእግዚአብሔር መሲሃዊ ንጉሥ መሆኑን ያለጥርጥ አረጋግጧል፡፡

ኢየሱስ ለንጉሥነት የመጣ ከሆነ፣ አልተሳካለትም ማለት ነውን? ይህ ጥያቄ በየዘመናቱ ያሉትን ክርስቲኖች እንደሚያስቸግር ሁሉ በስደት ላይ ያሉትን የማርቆስ ተደራሲያንንም ያስቸግራቸዋል፡፡ እንዲያውም፣ አሁን በምድር የኢየሱስን ንግሥና አናይም፡፡ መሲሃዊ ንጉሥ ሊያደርግ የተገባውን ሁሉ ያከናወነ አይመስልም፡፡

> **በማርቆስ ወንጌል፣ በወንጌሉ የመጀመሪያ ክፍል ውስጥ፣ የኢሱስ ንግሥና በብርቱ አፅንዖት ተደርጎበታል፣ ስለዚህም ኢየሱስ በበሽታ ላይ ኃይል ያለው መሆኑን ገልጧል፡፡ በተፈጥሮ ላይ ኃይል ያለው መሆኑን ገልጧል፡፡ የሚከተሉትን በዙሪያው ማሰባሰብ የሚችል መሆኑን ገልጧል፡፡ አምላካዊው-ንጉሥ በመካከላችን ሊያደርግ የተገባቸውን ሁሉ አድርጓል፡፡ በተለይም በማርቆስ ወንጌል ውስጥ ደቀመዛሙርቱ በቀላሉ ሊይዙት ያስቸገራቸው ነገር፣ ኢየሱስ ንጉሥ ነኝ ብሎ ተናግሮ ሳለ ንግግሩ ቀስ እያለ ወደ ልቡናቸው ሲሰርፅ፣ ወዲያው ደግሞ እንደሚናቅ፣ መከራ እንደሚቀበልና እንደሚሞት መናገሩ ነበር፡፡ እናም መጀመሪያ ላይ፣ እንደማስበው፣ ንጉሥ እንደ ሎሌ የመምጣቱ ነገር ለመጨበጥ በጣም አስቸጋሪ ሆኖባቸው ነበር፡፡ ሆኖም ግን ወደ ኋላ መለስ ብሎ የመቃኘትን ዕድል በመጠቀምና እንደ ኢሳያስ 53 የመሳሰሉትን ንጉሥ እንደሚመጣ የሚናገሩትን ክፍሎች ስታሰባስቧቸው፣ መከራን እንደሚቀበልና እንደሚሞት ይናገራሉ፡፡ ኢየሱስም ያንን የሚያደርገው የሰው ልጅ ኃጢአት ዕዳ ለመክፈል መሆኑን ያምናል፣ እናምበመስቀል ላይ ግርማዊነቱን በመተው የሰውን ዘር ኃጢአት ያስተሰርያል፡፡ በእርግጥ ያ የታሪኩ ፍፃሜ አይደለም ምክንያቱም ክርስቶስ ከሞት ተነሥቶ በሰማያት የፍጥረታት ሁሉ ገዢ በመሆን በክብር የንጉሥነት መንበር ላይ ተቀምጧል አንድ ቀንም በሕያዋንና በሙታን ሊፍድ ይመለሳል፡፡ (ዶ/ር ሲሞን ቫይበርት)**

ኢየሱስ በመጀመሪው ክፍለ ዘመን የነበሩ ሰዎች የሚጠብቁት ዓይነት መሲህ አልነበረም፣ ደግሞም በዚህም ዘመን ያሉ ሰዎች የሚፈልጉት ዓይነትም ሰው አይደለም፡፡ እርሱ የኖረው የመከራን አገልጋይነት ኑሮ ሲሆን የመንግሥቱንም ህዝብ የሚጠራው ተመሳሳዩን እንዲያደርጉ ነው፡፡ ስለ ዘሪውና ስለ ሰናፍጭዋ ቅንጣት በተናገረበት ምሳሌው ውስጥ፣ ተከታዮቹ መከራን እንደሚቀበሉ፣ ያም መንግሥቱ የተሸነፈች እንደሚያስመስላት አስተምሯል፡፡

በአንዳንድ ሰዎች ውስጥም የመንግሥቱ ቃል ስር እንደሚሰድና ፍሬን እንደሚፈራም አስተምሯል፡፡ እነርሱም የእግዚአብሔርን መንግሥት በመታዘዝ ይቀበሏታል፡፡ ኢየሱስንም በመከተል የእግዚአብሔርን ምገሥት ያሰፋሉ፡፡

የእግዚአብሔር መንግሥት ለጊዜው ትሰደባለች፤ የምታድገውም በዝግታ ነው፤ እንዲያውም መከራን ትቀበላለች፡፡ በስተመጨረሻው ግን፣ የእግዚአብሔር መንግሥት በሙላት ትመጣለች፡፡ ኢየሱስ በማርቆስ 4፥2 እንደተናገረው፡

> **እንዲገለጥ ባይሆን የተሰወረ የለምና፤ ወደ ግልጥ እንዲመጣ እንጂ የተሸሸገ የለም።**
> **(ማርቆስ 4፥22)**

ማርቆስ ለመጀመሪያዎቹ ተደራሲያንና ለእኛ ያስተላለፈወ መልእክት ግልፅ ነው፡፡ የእግዚአብሔር መንግሥት በምስጢር ታድጋለች፣ ከስደት፣ ከመከራና ከጠላቶች ጋር ትታገላለች፡፡ እንደ እግዚአብሔር የጊዜ ሰሌዳም በእርግጠኝነት ታድጋለች፡፡ የእግዚአብሔር መንግሥትና የኢየሱስ አገልግሎት ማንም ሊያቆመው አይችልም፡፡ አንድ ቀን፣ ኢየሱስ የጀመረውን ሊፈፅም ይመለሳል፡፡ ለአንዴና ለመጨረሻም ጠላቶቹን ድል ያደርጋል፣ እኛም እነከብራለን፣ ማብቂያ ወደ ሌለውም የዘላለም ሕይወት እንገባለን፡፡ በዚያን ጊዜ፣ አንድም ያልተፈፀመ የብሉይ ኪዳን ትንቢት አይኖርም፡፡ እርሱ ሁሉን ይፈፅማል፡፡

# ማጠቃለያ

በዚህ ትምህርት የማርቆስን ወንጌል ዳራ ከማርቆስ ጸሐፊነት፣ ከቀደምት ተደራሲያኑ እና ከተጻፈበት ወቅት አንፃር ተመልከተነዋል፡፡ የወንጌሉን ውቅርና ይዘትም ዳሰሰናል፡፡ በሁለቱ ዐቢይ መሪ ሃሳቦቹም ላይ ትኩረት አድርገናል፡፡ እነርሱም፡ የኢየሱስ ማንነት መከራን እንደሚቀበል አገልጋይ እና እንደ ንጉሥ ናቸው፡፡ እነዚህን ሃሳቦች በልቡናችን ይዘን ይህን ወንጌል ብናነብብ፣ የማርቆስን ወንጌል ሙሉ በሙሉ እንረዳለን እናም በዘመነኛው ዓለምም በተሻለ መንገድ ከሕይወታችን ጋር ልናዛምደው እንችላለን፡፡

የማርቆስ ወንጌል በሌሎቹ ወንጌላት አፅንዖት ያልተሰጠባቸውን የኢየሱስ ባህርይና አገልግሎት ገፅታዎች አስምሮባቸዋል፡፡ ኢየሱስንም እንደ ኃያል፣ የማይደከም፣ ንቁ የአካባቢው ጌታ አሳይቶናል፡፡ በተጨማሪም ኢየሱስ ያንን ኃይሉን ይዞ የአገልጋይ መሪነትን ሃላፊነት መወጣቱንም ያሳየናል፡፡ የጌታችንንም ምሳሌነት በመከተል የተለያዩ ምላሾችን እንድንሰጥ ማርቆስ ጥሪ ያደርግልናል፡፡ በኢየሱስ እግሮችም ስር በአድናቆት እንድንወድቅ፣ በጸጥታም እንድናደምጠው እና በፍፁም መታዘዝም ለቃሎቹ ምላሽ እንድንሰጥ ይፈልጋል፡፡ ኢየሱስ እንዳደረገውም፣ በፈቃዳችን ስለ እግዚአብሔር መንግሥት መከራን እንድንቀበልም ይፈልጋል፡፡ በመስቀል ላይ ኢየሱስ ጠላቶቹን ድል ሲያደርግ፣ ለእኛም ድሉን ያፀናልን መሆኑን በማወቅ እንድንበረታታም ይፈልጋል፡፡ ኢየሱስ በክብር መንግሥቱን በፍፃሜው ይዞ ሲመለስም ያንን ክብር እንደሚያጎናፅፈን በማመን እስከዚያ ቀን ድረስ በተስፋ ልንፀና ይገባናል፡፡